# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 136 ጥር 16 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# “የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ ማንም ሰው ኢንቨስተር እንዲሆን ዕድል የሚፈጥር ነው”

- እሌኒ ገብረመድህን (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ የቦርድ አባል

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- በቅርቡ በኢትዮጵያ የተጀመረው የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ ማንም ሰው ኢንቨስተር እንዲሆን ዕድል የሚፈጥር ነው ሲሉ የኢትዮጵያ የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ የቦርድ አባል እሌኒ ገብረመድህን (ዶ/ር) ገለጹ። ገበያው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እንደሚጨምርና የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር አመልክተዋል። እሌኒ (ዶ/ር) ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ በቅርቡ የተጀመረው የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ ሁሉንም ዜጋ አሳታፊና አካታች በመሆኑ ማንም ሰው ኢንቨስተር እንዲሆን ዕድል የሚፈጥር ነው። ገበያው ለትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የሌሎች ሀገራት ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ ለሚፈልጉ ሰፊ ዕድል የሚሰጥና የሥራ ዕድል የሚፈጥር መሆኑንም አመልክተዋል።

ብዙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና ስለኢትዮጵያ የሰሙ የሌሎች ሀገራት ዜጎች በትናንሽ ገንዘብም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ እየፈለጉ መንገድ አጥተው መቆየታቸውን አውስተው፤ አሁን ግን የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያው ስለተጀመረና በየትኛውም ሀገር የሚኖሩ ሰዎችን ስለሚያስተናግድ ትልቅ ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ይጎርፋል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ መከፈቱ እጅግ በጣም ደስ መሰኘታቸውን የሚገልጹት እሌኒ (ዶ/ር)፤ ከዚህ ቀደም የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ እንደነበረን እና አሁን እንደገና እንደተጀመረ ተደርጎ የሚነገረው ትክክል አይደለም። የሰነደ መዋለ ነዋዮች ገበያው ለመጀመሪያ ጊዜ የተጀመረ እና አዲስ ነገር መሆኑን ተናግረዋል።

የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያው ውጤታማ ይሆናል

“የሰነደ መዋለ ንዋዮች... ወደ ገጽ 4ዞሯል



ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ



ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መላኩ ፈንታ

## የዲጂታል ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ለፖሊስ ሥራ ውጤታማነት ጉልህ ሚና መጫወታቸው ተገለጸ

- የደህንነት ካሜራዎችም ለወንጀል ምርመራ ጥራትና ፍጥነት አቅም ሆነዋል

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ሪፎርሙን ተከትሎ እየተከናወኑ ያሉ የዲጂታል ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶች ሥራዎች ለፖሊስ ተግባር ውጤታማነት ጉልህ ሚና እንዳላቸው የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ አስታወቀ። የመንገድ ዳር የደህንነት ካሜራዎች እና ዲጂታል የሞባይል መተግበሪያውም ለወንጀል ምርመራ ጥራትና ፍጥነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆኑም ተጠቁሟል። የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ትናንት ለጋዜጠኞች ባዘጋጀው የጉብኝት መርሀ ግብር ላይ ተገኝተው ንግግር

የዲጂታል ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

## ካዛንችስን መልሶ በማልማት ሁለት ሺህ የንግድ ሱቆችና 20 ሺህ የመኖሪያ ቤቶች ይገነባሉ

ገጽ 3

# በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከ127 ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል

-ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የበላይ አመራሮች ሹመት አጸደቀ

**ዓመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ስድስት ወራት ለ127 ሺህ 385 ዜጎች የሥራ እድል መፈጠሩን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ። የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ16ኛ መደበኛ ስብሰባው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን የ2017 በጀት ዓመት የ6 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርትን ትናንት ግምገማ ማካሄዱን እና የዕንባ ጠባቂ ተቋም የበላይ አመራሮችን ሹመት ማጽደቁ ተገልጿል። በወቅቱ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በስድስት ወራት ለ125 ሺህ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፤ ለ127 ሺህ 385 ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሯል።አፈጻጸሙ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት



ጋር ሲነጻጸር የአምስት ነጥብ አምስት በመቶ ብልጫ አሳይቷል ብለዋል። የወጪ ምርት ከማሳደግ አኳያም 117 ሺህ 586 ቶን የምርት መጠን ለመላክ ታቅዶ፤ 95 ሺህ 167 ቶን ለመላክ መቻሉን አመልክተው፤ ይህም አፈጻጸሙ 80 ነጥብ 93 በመቶ ሲሆን፤ ባለፈው ዓመት መላክ

በአምራች ኢንዱስትሪው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# በባቱ ከተማ ከሰባት ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ተሸፈነ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በ2017 ምርት ዘመን ከሰባት ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ መልማቱን የባቱ ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽህፈት ቤት አስታወቀ። የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ለሚ ኩርሶ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው ዓመት ስምንት ሺህ 500 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት ታቅዶ እየተሠራ ነው።እስከ ጥር 13 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስም ሰባት ሺህ 046 ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለምቷል።

በቀጣይነትም የደረሱ ሌሎች ምርቶችን በማንሳት ቀሪውን ስንዴ ለማልማት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ሥራው በአብዛኛው የሚሠራው በኩታ ገጠም (በክላስተር) መሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል ለማድረግ አመቺ ሁኔታ መፍጠሩን ተናግረዋል።የበጋ ስንዴው የለማው በኩታ ገጠም መሆኑም ሰብሉን ከግሪሳና ሌሎች ተባዮች ለመከላከል፣ ትራክተርን በአግባቡ ለመጠቀም እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ በትብብር ለመሥራት ያስችላል ብለዋል።

በአካባቢው የከተማ ግብርና ከዚህ በፊት በስፋት የሚተገበር እንዳልነበር አስታውሰው፤ በዚህም በተወሰነ መልኩ የግብዓት ችግር ያጋጥማል። ችግሩን ለመቅረፍም ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።የአርሶ አደሩ ውጤታማነትና የተቀመጡ ፕሮግራሞችን ተቀብሎ በመተግበር በኩል ከፍተኛ ውጤት እየተመዘገበ ነው ያሉት ለሚ (ዶ/ር)፤ በከተማ አስተዳደሩ ሥር ከሚገኙ አስር ቀበሌዎች ውስጥ ሰባቱ በስንዴ ልማት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል።



ይህንን መልካም ተሞክሮ ወደ ሌሎችም ለማስረጽና ለማስፋፋት የተሞከሮና ልምድ ልውውጥ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑንም አመላክተዋል። ከዚህም በተጨማሪ በግብርና ሥራቸው ከፍተኛ ውጤት ያመጡ አርሶ አደሮች በከተማ መሬት ተሰጥቷቸው ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ መደረጉን ጠቁመው፤ ይህም ሌሎች አርሶ አደሮችን በማነሳሳት ለውጤታማነት ትኩረት ሰጥተው እንዲሠሩ በማድረግ በኩል ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

የደምበል ሀይቅ በከተማው መሐል መገኘት ለከተማ ግብርና ሥራው ትልቅ አቅም መሆኑን ጠቁመው፤ የአርሶ አደሩ በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ የማምረት ልምድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል።ይህም የማህበረሰቡን ሕይወት ለመለወጥና ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንደሀገር የተያዘውን እቅድ ከማሳካት አንጻር ትልቅ ትርጉም እንደሚኖረው አመልክተዋል። አርሶ አደሩን በውጤት እንዲታጀብ ለማድረግ የግብርና ባለሙያዎችና በየደረጃው ያለው አመራር አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርጉ ለሚ (ዶ/ር) ጨምረው ገልጸዋል።

## በቀጣዮቹ ቀናት አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ዝናብ እንደሚያገኙ ተጠቆመ

**ነፃነት አለሙ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣዮቹ አስር ቀናት አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ዝናብ እንደሚያገኙ የኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የላከው መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ለዝናብ መፈጠር አስተዋፅኦ ያላቸው የሚቲዎሮሎጂ ገፅታዎች በቀጣዮቹ አስር ቀናት ላይ ተጠናክረው ይቀጥላሉ። በዚህም በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛውና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ።

በመጪዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ፀሐያማውና ነፋሻማው አየር እንደሚቀጥል የጠቆመው ትንበያው፤ አርሶ አደሮች በእነዚህ ቀናት ሰብሎችን አጠናቆ የመውቃትና የማጓጓዝ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ አሳስቧል።

በተለይም የበልግ ወቅት እርሻ ከመቃረቡ ጋር ተያይዞ የሰብል ማሳዎችን ከማንኛውም ተረፈ ምርት ነጻ የማድረግና ለዘር የማዘጋጀት ሥራዎችን መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁሟል። በተጠቀሱት ቀናት የመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት በላይኛውና በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛው አሞ ግቤ እና አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ ርጥበት እንደሚኖር ተጠቁሟል።

ይህም ለውሃ ሀብት መሻሻል አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ተመላክቷል። ባለፉት አስር ቀናት የመጨረሻ ቀናት ላይ ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተጠናክሮ እንደነበር ያስታወሰው ትንበያው፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝቅተኛው የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ መመዝገቡን ጠቁሟል።

በእነዚህ ቀናት የነበረው የዝናብ መጠንን በተመለከተም አማን፣ ጂንካ፣ ማጀቴ፣ ማይጨውና ኮምቦልቻ የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ እንደነበራቸው አመላክቷል።

ከመደበኛው ጋር ሲነፃጸር ከጥቂት የሰሜን ምሥራቅ ቦታዎች በስተቀር ከመደበኛ በታች የዝናብ መጠን እንደነበር አስታውሷል።

ባለፉት አስር ቀናት የነበረው ደረቃማ የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛው፣ የደቡብና የምሥራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አንፃራዊ ጥንካሬ እንደነበረው ትንበያው ያሳያል።

በአንዳንድ አካባቢዎችም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት ከአምስት ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ መመዝገቡን ጠቁሟል።

የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማጠናቀቅ ግን በአመዛኙ በጎ ጎን እንደነበረው ተመላክቷል።

በእነዚህ አስር ቀናት ሁሉም ተፋሰሶች የበጋው ደረቅ ሁኔታ ስር እንደቆዩ የውሃ መረጃዎች እንደሚያመለክቱም ትንበያው አስታውሷል።

# ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማር ባሻገር ለስፖርቱም ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው

### - የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የስፖርት ፌስቲቫል ነገ ይጀምራል

**ቦጋለ አበበ**

አዲስ አበባ፡- ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን ለስፖርት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ገለጸ።ለዘጠኝ ዓመታት ተቋርጦ የነበረው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የስፖርት ፌስቲቫል በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አስተናጋጅነት ነገ የሚጀምር መሆኑ ተጠቆመ።የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ደረጄ እንግዳው(ዶ/ር) በዩኒቨርሲቲው አስተናጋጅነት የሚጀመረውን የተማሪዎች ስፖርት ፌስቲቫል አስመልክተው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ ዩኒቨርሲቲው ፌስቲቫሉን ማስተናገድ የሚያስችሉ ዝግጅቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፤ እንዲህ አይነት ፌስቲቫሎችን በተሟላ ሁኔታ ለማስተናገድ ዩኒቨርሲቲው አነስተኛ ስቴድየምና ሌሎች የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ያስፈልጉታል።ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎንም ለስፖርቱ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው።የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ፌስቲቫሉን ለማስተናገድ የነበረው ጊዜ አጭር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደ አንጋፋዎቹ ዩኒቨርሲቲዎች የአነስተኛ ስቴድየምና የበርካታ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ትሩፋት ተጠቃሚ አለመሆኑን ተናግረዋል።

ቀደም ባሉት ዓመታት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የስፖርት ውድድር ለማስተናገድ እንደ አዳማና ጅማ ያሉ አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች የአነስተኛ ስቴድየሞችና የተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ባለቤት መሆናቸውን አስታውሰው፤ እነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ስቴድየሞቹን ሲገነቡ፤ ግንባታው በገንዘብ ሚኒስቴር ጭምር የሚደገፍና ከዓመት በፊት ዝግጅት የሚደረግበት እንደነበር አስታውሰዋል።

ዩኒቨርሲቲዎቹ ባገኙት ትሩፋት ከራሳቸው አልፎ እንደ ኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ያሉ ትልልቅ ሀገራዊ ውድድሮችን ለማስተናገድ በቅተዋል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አነስተኛ ስቴዲየም እና የተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን መገንባት ቀጣይ እቅዶቹ እንደሆኑ ጠቁመው፤ አነስተኛ ስቴድየሙን የመገንባት እቅድ ብቻ ሳይሆን ፍቃድም እንዳለው ተናግረዋል።

በዩኒቨርሲቲው የሚገነቡት የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችም ከግቢው ተማሪዎች ባሻገር ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚያገለግሉ ይሆናሉ ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው አሁን ላይ የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚያሳልጡ ግንባታዎችን ለማጠናቀቅ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ከእነዚህም መካከል በአፍሪካ ደረጃ ትልቅ የሆኑ ስምንት የሳይንስና ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከላት እንደሚገኙ ጠቅሰዋል።

የተጀመሩ ግንባታዎችን በአጭር ጊዜ አጠናቅቆ ፊቱን ወደ አነስተኛ ስቴድየምና የስፖርት ማዘውተሪያ ግንባታዎች በማዞር እቅዱን እውን እንደሚያደርግ አስረድተዋል።

“ለመማር ማስተማር ሂደቱ ቅድሚያ ለመስጠት ነው እንጂ ስፖርቱ ያስፈልገናል” ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ዩኒቨርሲቲው ሳይንስና ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ያደረገ ቢሆንም ከማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ በተጨማሪ ለስፖርት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። ቀደም ባሉት ዓመታት ስፖርት ከመደበኛ የመማር ማስተማር ሂደት ወጥቶ እንደነበር በማስታወስም፤ ከአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ በኋላ አንዱ የሥርዓተ ትምህርት አካል መሆኑን ተናግረዋል።

ይህም ትልቅ ለውጥ እንደሆነና የስፖርቱን ዘርፈ ብዙ ትሩፋት ለመጠቀም እንደ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የስፖርት ትምህርት ክፍል ለሌላቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እድል ፈጥሯል ብለዋል። በዚህም ምክንያት ዩኒቨርሲቲ የገባ ተማሪ ሁሉ ስፖርትን በፅንሰ ሃሳብም በተግባርም ሳይማር እንደማይወጣ ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

ስፖርት ገፅታን በመገንባት ረገድ ያለውን ፋይዳ ያብራሩት ፕሬዚዳንቱ፤ በዚህም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለሌላው ማህበረሰብ ምሳሌ እንዲሆኑና ማህበረሰቡም ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በጎ አመለካከት እንዲኖረው ያደርጋል ሲሉ ፕሬዚዳንቱ አስረድተዋል።



# ካዛንችስን መልሶ በማልማት ሁለት ሺህ የንግድ ሱቆችና 20 ሺህ የመኖሪያ ቤቶች ይገነባሉ

**በሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ካዛንችስን መልሶ በማልማት በተገኘ 800 ሄክታር መሬት ላይ ሁለት ሺህ የንግድ ሱቆች እና 20 ሺህ የመኖሪያ ቤቶች እንደሚገነቡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አመለከቱ።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመንግሥት እና በግል አጋርነት የሚሠራ መኖሪያ ቤቶች የማስጀመሪያ መርሀ ግብር ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ካዛንችስ ከመልሶ ማልማት በፊት ስምንት ሺህ የመኖሪያና የንግድ ቤቶች በጥቅሉ ወደ 21 ሺህ ሰዎች የሚኖሩበት አካባቢ ነበር። በመልሶ ማልማት ሥራ ሁለት ሺህ የንግድ ሱቆች እና 20 ሺህ የመኖሪያ ቤቶች ይገነባሉ። በዚህም አካባቢው ከ100 ሺህ በላይ ሰዎች የሚኖርበት አካባቢ ይሆናል ብለዋል።

ካዛንቺስ ላይ የምንገነባው ማህበራዊ ግልጋሎትን የሚሰጡ ተቋማትን ጨምሮ የመማሪያ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማትን፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን፣ አረንጓዴ ቦታዎችን፣ ሞሎችን፣ ሱቆችን እንዲሁም ሰፋፊ የመኪና ማቆሚያዎችን ያካተተ ግዙፍ ፕሮጀክት እንደሆነ ተናግረዋል።

በከተማችን ያረጁ እና ለመኖር ምቹ ያልሆኑ እንደ ካዛንቺስ ያሉ አካባቢዎችን መልሰን ስናለማ በዋነኛነት የሕዝቡ ዋነኛ አንገብጋቢ ጉዳይ የሆነውን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ለመመለስ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ የመኖሪያ ቤቶችን ስንገነባ ቤት ብቻ ሳይሆን ለኑሮ ምቹ የሆነ አካባቢንም ጭምር እንደሆነ ገልጸዋል።

በካዛንቺስ ኮሪደር ልማት ሰባት መንገዶች እየተገነቡ ነው። እነዚህ መንገዶች በሚቀጥሉት ሁለት ወራት እንደሚጠናቀቁ ጠቁመው፤ መኖሪያ ቤት አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ይህንን ለመመለስ የሕግ ማሻሻያ ተደርጓል። በዚህም ቤቶችን ለመገንባት በርካታ አማራጮች ቀርበዋል ነው ያሉት።

እነዚህም በመንግሥት፣ በመንግሥትና በግል፣ በማህበር እና በሪል ስቴት የሚገነቡ ቤቶች ተጠቃሽ መሆናቸውን አንስተው፤ በእነዚህ አማራጮች እስከ አሁን 270 ሺህ ቤቶች ተገንብተዋል። የቤት አቅርቦቱን በማስፋት አብዛኛውን ሕዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

አዲስ አበባ ንጹህ፣ ፅዱ፣ ለነዋሪዎቿ ምቹ እና ተወዳዳሪ የሆነች ዓለም አቀፍ ከተማ መገንባታችንን አሁንም አጠናክረን ቀጥለናል ሲሉ ተናግረዋል።

የአያት አክሲዮን ማህበር ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ዐቢይ ማሞ፤ "የካሳንቺስ አያት መኖሪያ መንደር" 13 ሺህ 752 የመኖሪያ ቤቶች በውስጡ እንዳሉት ገልጸዋል።

በዚህ የተለያዩ ስፋት ያላቸው መኖሪያ ቤቶች፣ ንግድ ማዕከላት፣ የሕዝብ መሰብሰቢያ ፕላዛዎች፣ የልጆች መጫወቻ እና የስፖርት ማዘውተሪያዎችን፣ ሙአለ ሕፃናቶች፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋማት፣ የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶችን፣ የመኪና ቻርጂንግ ስቴሽኖች፣ የመኪና እና የብስክሌት ፓርኪንግን አካቶ በከፍተኛ ጥራት እና ፍጥነት የሚገነባ ይሆናል ብለዋል።

# የማዕከሉ የእንክብካቤና ጥበቃ ሥራ የእንስሳት ቁጥር እንዲጨምር እያደረገ ነው

**ስምስም መንግሥቱ**

አዲስ አበባ፡- ማዕከሉ በየጊዜው በሚደረግለት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ የተለያየ ዝርያ ያላቸው የዱር እንስሳት ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን የጉለሌ እጽዋት ማዕከል ገለጸ።

የጉለሌ እጽዋት ማዕከል የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ያሬድ ጌታሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በየጊዜው በጥናት ላይ ተነስተው እየተከናወኑ ባሉ ሥራዎች ለውጦች እየተመዘገቡ ነው። በዚህም የዕፅዋት ተለያይነት (ዳይቨርስቲ) ጨምሯል።

የዕፅዋት ተለያይነት መጨመር ደግሞ ለእንስሳት መጨመር ምክንያት መሆኑን አመልክተው፤ በአሁኑ ጊዜ አካባቢው ላይ ይኖራል ተብሎ የማይጠበቀው ነብር ይገኛል። የምኒልክ ዱኩላ፣ ከርከሮ፣ የዱር አሳማ፣ አሞራ፣ ሰስ በማዕከሉ ውስጥ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል።

ብርቅዬዎችን ጨምሮ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአእዋፋት ዝርያዎችም እንደሚገኙ ጠቁመው፤ይህም የመጣው በማዕከሉ በሚሠሩ ውጤታማ ሥራዎች እንደሆነ ገልጸዋል።

‹‹ማዕከሉ ለአዲስ አበባ ከተማ ሳምባ ሆኗል። መልእክታችን እጽዋትን ይመልከቱ፤ ንፁህ አየር ይተንፍሱ ሆኗል።›› ያሉት አቶ ያሬድ፤ እንዲህ ያለውን ለውጥ ማስመዝገብ የተቻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያልተቋረጠ ድጋፍና ክትትል በመኖሩ እንደሆነ ተናግረዋል።

የማዕከሉን መሠረተ ልማት ለማሟላት እየተከናወኑ ካሉ ሥራዎች አንዱ የውሃ መሠረተ ልማት መሆኑን የጠቀሱት አቶ ያሬድ፤ ለእጽዋቶች እንክብካቤና ጥበቃ የገፀ ምድርና ከርሰምድር ውሃ ጥቅም ላይ እንደሚውል ገልጸዋል።



**የማዕከሉ ከፊል ገጽታ፤**

የውሃ አቅርቦቱን ለማሳደግ የውሃ ፕሮጀክት ጥናት ሥራ መጠናቀቁንና በጥናቱ መሠረት ወደ 70 ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ እንደሚመነጭና ይህም ለማዕከሉ አስተማማኝ የውሃ ፍላጎት ለማሟላት ያግዛል ብለዋል።

በመንገድ መሠረተ ልማት በኩልም 21 ኪሎ ሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገድ በድንጋይ ንጣፍ(ኮብል ስቶን) እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ ይህም መሠረተ ልማት ለማዕከሉ ከሚሰጠው ውበት በተጨማሪ በእጽዋት ማዕከሉ ውስጥ ለሚከናወኑ ሥራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸዋል።

በማዕከሉ ውስጥ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚሰበሰቡት እጽዋቶች በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ፣ ብርቅዬ የሆኑና ዝርያቸው ለመጥፋት በአደጋ ውስጥ የሚገኙ ሀገር በቀል የእጽዋት አይነቶች ላይ ትኩረት እንደሚደረግ አስረድተዋል።

እጽዋቶቹ በማዕከሉ ውስጥ የየራሳቸው ቦታ እንዲኖራቸው በማድረግ እንክብካቤና ጥበቃ ይደረግላቸዋል ብለዋል።

ለምግብነት ከሚውሉ እጽዋቶችም ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የእንሰት ችግኝ መጥቶ በማእከሉ እንዲፀድቁ በማድረግ በአራት ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ 64 የሚሆኑ የእንሰት ዛፍ ማድረስ መቻሉንና ችግኞችንም የማፍላት ሥራ መከናወኑን አመልክተዋል።

ማዕከሉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋራ ጥረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ባሳለፈው ውሳኔ በ2000 ዓ.ም መንግሥታዊ ተቋም ሆኖ መቋቋሙ ይታወሳል።

ማዕከሉ ሲቋቋም ከተሰጠው ተልእኮም የሀገሪቱን የእጽዋት ዝርያዎች መጠበቅ፣ መንከባከብ ነው። እንዲሁም በሀገሪቱ የእጽዋት ዝርያዎች ምርምርና ጥናት እንዲካሄድ ለትምህርት ቤቶችም የብዝሃ ህይወት ተግባር ተኮር የትምህርት አገልግሎት እንዲሰጥ፣ የእጽዋት ማዕከሉ መሠረተ ልማትና ተፈጥሮአዊ ነገር በመጠቀም ከተፈጥሮ ጋር የተስማማ የመዝናኛ አገልግሎቶችን መስጠት የሚሉት እንደሚጠቀሱ ይታወቃል።

# የበይነመረብ ቀጥታ ግብይት አዳዲስ ምርቶች ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የበይነመረብ ቀጥታ ግብይት አዳዲስ ምርቶች ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ የሚያደርግ፣ ምጣኔ ሀብትን የሚያሳድግና ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን የሚያደርግ እንደሆነ ተጠቆመ።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የበይነመረብ ቀጥታ ግብይት ሥርዓት ትናንት ሲያስተዋውቅ ባለ24 ወለል ሕንፃ ለመገንባት መሰረተ ድንጋይ አስቀምጧል፤ ይጠቀምበት የነበረውንም ሎጎ ቀይሯል።

በትውውቅ ፕሮግራሙ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)፤ የበይነመረብ ቀጥታ ግብይት አዳዲስ ምርቶች ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ የሚያደርግ፤ የውጪ ግብይትን የሚያሳድግ፤ ብሄራዊ ህልውናን የሚያረጋግጥና ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን የሚያደርግ የማዕዘን ድንጋይ ነው ብለዋል።

የበይነመረብ ቀጥታ ግብይት ተገበያዮች ባሉበት ቦታ ሆነው እንዲገበያዩ የሚያደርግ መሆኑን ጠቁመው፤ የግብይት ሥርዓቱ ፍትሐዊ፣ ተወዳዳሪ፣ ተደራሽና አካታች እንዲሆን የሚያደርግ እንደሆነም ገልጸዋል።

የንግዱን ዘርፍ ተግዳሮቶች ለመፍታት ወቅቱን የጠበቀ የፖሊሲና የመመሪያ ማሻሻያ መደረጉና ተያያዥ ሥራዎች በመሠራታቸውም የውጪ ንግድንና ኢንቨስትመንቱ ላይ ትልቅ ውጤት እየታየ መሆኑን ተናግረዋል።

የበይነመረብ ግብይት ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ትልቅ ሚና አለው፤ የተገበያዮችን ድካምና ጊዜ የሚቆጥብ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ ግብይትን የሚፈጥር ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንድምአገኘሁ ነገራ በበኩላቸው፤ የብይነመረብ ቀጥታ ግብይት የውጪ ንግድን የሚያሳድግ ነው። የኢትዮጵያ የግብይት ሥርዓት ኋላቀር ነው፤ ግብይቱን የማዘመን ሥራ እየተሠራ ነው፤ ይፋ የተደረገውም የብይነመረብ ቀጥታ ግብይት አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል።

የበይነመረብ ቀጥታ ግብይት ተደራሽነትን፣ አሳታፊነትን፣ ግልጸኝነትንና ፍትሐዊነትን የሚያሰፍን ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የተዋወቀው የበይነመረብ ቀጥታ ግብይት ተገበያዮች ባሉበት ቦታ ሆነው እንዲገበያዩ የሚያስችል፤ ጊዜን፣ ጉልበትን የሚቆጥብ፤ ደላላዎችን ከገበያው በማስወጣት አርሶ አደሩን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ጨው፤ የቆዳ ሌጦ፤ ጥጥ፤ ያለቀላቸው የኢንዱስትሪ ምርቶች በበይነመረብ ቀጥታ ግብይት ለተገበያዮች እንደሚቀርቡ ጠቁመው፤ በይነመረቡ አዳዲስ ምርቶችን ወደ ዲጂታል ግብይት እንዲካተቱ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት ተልባን፣ የቢራ ገብስንና መሰል ምርቶችን ወደ በይነመረብ ግብይት የማካተት ሥራ ተሰርቷል። በቀጣይም ጨው፣ ሌጦን ፣ ጥጥና ሌሎች ምርቶችን ይካተታሉ ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለፉት 17 ዓመታት ስምንት ሚሊዮን ቶን ምርት ለግበይት በማቅረብ 401 ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ገቢ አግኝቷል፤አራት ነጥብ 5 ሚሊዮን አርሶ አደሮችንም ተጠቃሚ አድርጓል ሲሉ ገልጸዋል።

ዜና

# “የሰነደ መዋለ ንዋዮች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚል ትልቅ እምነት አለን ያሉት እሌኒ (ዶ/ር)፤ መጀመር ከነበረብን ጊዜ ዘግይተናል እንጂ ገና ነን አንልም። ከተለያዩ ሀገራት ተሞክሮ ልምድ በመውሰድ አቅማችንን አሳድገን ዝግጅት አድርገን ነው የጀመርነው። ከውጭ ሀገራት ተሞክሮዎች ብዙ ልምድ የወሰደ ጠንካራ ባለሥልጣን ድርጅት መፈጠሩ ትልቅ መተማመኛ የሚሰጥ ነገር ነው ብለዋል።

እስካሁን ባለው አሠራር ሰዎች ድርሻ የሚገዙትና የሚሸጡት ከሚያውቁት ሰው ወይም ባንክ ሄደው ነው። ይሄ ደግሞ ጊዜ የሚወስድ እና ውጤታማ ያልሆነ መሆኑን ገልጸው፤ ሁሉም ሰው ድርሻ መግዛትና መሸጥ የሚችልበት የጋራ መገበያያ መድረክ እንዲሁም ግልጽ ዋስትና የሚሰጥና ቀልጣፋ የሆነ የግብይት ሁኔታን መፍጠር አለበት። ገዢዎቹን እና ሻጮቹን የምናውቅበት የተደራጀ የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ ያስፈለገንም ለዚህ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ቀጣዩ ሥራ ገበያውን በስፋት ከሕዝብ ጋር ማስተዋወቅ መሆኑን የጠቆሙት እሌኒ (ዶ/ር)፤ የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያ ማንም ሰው ኢንቨስተር እንዲሆን ዕድል የሚፈጥር ነው። በእኛ በኢትዮጵያኖች አመለካከት ኢንቨስተር ሲባል ትልቅ ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ ሰዎችን ብቻ ነው የምናስበው። ነገር ግን ትናንሽ ድርሻዎችን ከኢትዮ ቴሌኮም ወይም ከሌሎች ድርጅቶች የገዛ ዜጋም ኢንቨስት አድራጊ ነው። የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያው ለእያንዳንዱ ዜጋ ትልቅ ሀብት የማጎልበቻ መንገድ እንደሆነ አብራርተዋል።



እሌኒ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ አነስተኛ መጠን ያለው ገንዘብ መቆጠብ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ወደ ባንክ ነው የሚሄዱት። ገንዘቡን በባንክ ሲያስቀምጡት በዓመት የሚያገኙት ስምንት በመቶ ወለድ ነው። ይህ የወለድ መጠን የባንክ ሼር በመግዛት ከሚያገኙት 30 በመቶ ትርፍ አንጻር አነስተኛ ነው።

ገንዘብን በባንክ ውስጥ ከማስቀመጥና የሚያድግ ሼር ለመግዛት ኢንቨስት ከማድረግ የትኛው እንደሚሻል ለእያንዳንዱ ሰው የሚተው ውሳኔ መሆኑን ያመላከቱት የሰነደ መዋለ ንዋዮች ገበያው የቦርድ አባሏ፤ ጥቅሙ እንደተጠበቀ ሆኖ ምርጫ መኖሩ ጥሩ ነገር ነው ብለዋል።

# በአምራች ኢንዱስትሪው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከተቻለው 74 ሺህ 954 ቶን ጋር ሲነጻጸር፤ የ26 ነጥብ 9 በመቶ እድገት ተመዝግቧል ሲሉ አስረድተዋል።

ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ ከውጭ ምንዛሬ ግኝት አንጻርም 256 ሚሊዮን 690 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 149 ሚሊዮን 334 ሺህ 400 ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ተችሏል።ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት የምንዛሪ ግኝት ጋር ሲነጻጸርም 6 ነጥብ 43 በመቶ ብልጫ አሳይቷል።

የተላከው ምርት አፈጻጸም ከፍተኛ ሆኖ፤ የምንዛሪ ግኝቱ ዝቅ ያለው በተለያዩ ምክንያቶች መሆኑን አቶ መላኩ ጠቁመው፤ ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች በዋጋ ዝቅተኛ ሆነው ስለሚወጡ ነው።

ይህን ችግር ለመቆጣጠር ወደ ውጭ በሚላኩ 29 ምርቶች ላይ ዝቅተኛ የዋጋ መጠን በጥናት በመተመን ተግባራዊ እየተደረገ ነው ብለዋል።

ዓለም አቀፍ የማጓጓዣ ዋጋ ግሸበት፣ የባሕር ትራንስፖርት እንቅስቃሴ ስጋት የተነሳ ወደ አውሮፓ ሀገራት ምርቶችን ለማድረስ ከዚህ በፊት 45 ቀናት የሚወስድ ሲሆን፤ አሁን ወደ 65 ቀን እንዲሆን አስገድዷል። ይህም በወጪ ምርት ተወዳዳሪነት ላይ ተጽእኖ በማሳደሩ፤ የምንዛሪ ግኝትን ከማሳደግ ረገድ ተግዳሮት መሆኑን አስረድተዋል።

ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ተኪ ምርት ከማሳደግ አንጻር በግማሽ ዓመቱ፤ አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ቶን የምርት መጠን ለመተካት ታቅዶ፤ አንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ቶን ተተክቷል። በዚህም ሁለት ቢሊዮን 71 ሚሊዮን ዶላር ማዳን ተችሏል።

የኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አማረች በካሎ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የኢንዱስትሪዎችን የቴክኖሎጂ አቅም በማጎልበት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ በትኩረት ሊሠራ ይገባል።

ከኢንዱስትሪዎች ስርጭት እና በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የሚመረቱ ምርቶችን ብራንዳቸውን ለማሳደግና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ለማትረፍ መሥሪያ ቤቱ ከታች ጀምሮ መሥራት እንዳለበት ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ምክር ቤቱ ወይዘሮ ስመኝ ውቤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዋና ዕንባ ጠባቂ፤ የኔነህ ስመኝ (ዶ/ር) ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ እና አቶ አባይነህ አዴቶን የዘርፍ ዕንባ ጠባቂ ሆነው መሾማቸውን በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

ZTE | nubia

ዜድቲኢ ኮርፓሬሽን በኢትዮጵያ ላለፉት 2 አስርት ዓመታት በስፋት በኔትወርክ ዝርጋታ በመስራት ላይ የሚገኝ ተቋም ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ዘመናዊ Smart ስልኮችን በማቅረብ ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያዊያን ደንበኞቹ በአይነቱ ልዩ የተባለለትን ZTE nubia focus pro 5G ዘመንኛ ስልኩን ለደንበኞቹ በይፋ አስተዋውቋል።

ይህን ዘመንኛ ስልክም ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር ወደ ገበያ ያስገባ ሲሆን ይኸው ስልክም መጪውን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ የተለያዩ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ገፅታዎችን ፥ የ AI translation እና gaming experience Ai Neo Vision imaging ከላቀ የፎቶ ካሜራ ጥራት ጋር ተመርቶ የቀረበ መሆኑን ጭምር ለማወቅ ተችሏል !!

zte ኢትዮጵያ ሌላም አዲስ ነገርን ይዞ መጥቷል። ከጥር 12, 2017 ዓ ም ጀምሮ ደግሞ የተመረጡ ስልኮቹን 10 % ቅድመ ክፍያ ብቻ በመክፈል ቀሪውን በብድር መልክ ለሽያጭ የሚቀርብበትን ልዩ የግዢ አማራጭ ጭምር ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር ይዞ እንደመጣ ተገልጿል።



ዜድቲኢ ኮርፓሬሽን በኢትዮጵያ

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደር ውጤቶችን ማላቅ፣ ችግሮችንም ማረም ይገባል

በአንድ ሀገር የሚኖር የመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደር፣ በዜጎች እና መንግሥት መካከል ያለውን ጉድኝት በማጠናከርም ሆነ በማላላት በኩል የማይተካ ሚና አለው። ምክንያቱም ሕዝብ መንግሥትን እንዲያስተዳድረው ሲመርጥና በላዩ ላይ ሲሾም፤ ያገለግለኛል፣ ያስተዳድረኛል፣ ጥያቄዎችና ፍላጎቶቼን ተገንዝቦ ምላሽ እና መፍትሔ ይሰጠኛል በማለት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ጠንካራ የመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደርን እውን ያደረጉ ተቋማትን የገነቡ ሀገራት መንግሥታት ሕዝቦቻቸውን ለሀገራዊ የልማቱም ሆነ የሰላምና ደህንነት አቅም አድርገው ሲራመዱ፤ በአንጻሩ ጠንካራ የአገልግሎትና አስተዳደር ሥርዓትን እውን ያላደረጉ ሀገራት መንግሥታት ሕዝቦቻቸውን ማስተባበር ተስኗቸው ተቃውሞዎችን ሲያስተናግዱ ማየትም የተለመደ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ሩቅ መሄድ ሳያስፈልገን፤ ወደ ጎረቤትም ማማተር ሳይኖርብን እዚሁ በቤታችን ውስጥ በዘመናት ውስጥ የሆነውን መለስ ብሎ መቃኘቱ በቂ አብነት ይሆናል። ለምሳሌ፣ የ2010ሩ ለውጥ ገፊ ምክንያት ከሚባሉት መካከል የመልካም አስተዳደር ችግርን መመልከት ይቻላል፡፡

የመልካም አስተዳደር ችግር ደግሞ ብዙ መልኮች አሉት። አንድም ዜጎች ከመንግሥታቸው ማግኘት የሚፈልጉትንም ሆነ የሚገባቸውን ነገር ማግኘት አለመቻላቸው አንዱ ሲሆን፤ ይሄ ደግሞ ጠንካራ እና የሕዝብ አገልጋይነትን የተላበሱ ተቋማት፣ አመራሮችና ባለሙያዎች በልካቸው ሆኖ አለመገኘት ውጤት ነው፡፡

አንድ ተቋም ደግሞ መሪውን ይመስላል። ምክንያቱም ተቋምን ተቋም የሚያስብሉት በውስጡ ያሉ የተቋሙ ኃላፊዎች እና በየደረጃው ያሉ ባለሙያዎች ናቸው። እነዚህ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ታዲያ በአግባቡ የተሰጣቸውን የኃላፊነትም ሆነ የሙያ ግዴታ መወጣት ከቻሉ፤ ተቋሙ እንደ ተቋም የሕዝብ አገልጋይነቱን ሲያረጋግጥ፤ ካልተወጡ ግን ውጤቱ በተቃራኒው ሆኖ ይገለጣል፡፡

ይሄ ኃላፊነትን ያለመወጣት ጉዳይ ታዲያ፣ አንድም ከአቅም ማነስ፤ ካልሆነም ተልዕኮን ካለመገንዘብ፤ አለፍ ሲልም ካልተገባ ባህሪና ጥቅም መፈለግ ጋር ሊያያዝ ይችላል። ለምሳሌ፣ የተቋማት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያሳዩት ያልተገባ ባህሪ እና ጥቅም የመፈለግ ሃሳብና ተግባርም የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በሙስና ገጽ ቀርጾ የሚያጠለሽ፤ ዜጎችም በመንግሥት ላይ ምሬትን እንዲያሰሙ፤ ሙሰኞች በልዩ ሁኔታ ያልተገባ ጥቅምን እንዲያግበሰብሱ የሚያደርግ ነው፡፡

በኢትዮጵያም ለ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ እውን መሆን ምክንያቶችም አንዱ ይሄው የዜጎች በመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደር ላይ ያነሱት ከፍ ያለ ቅሬታና ቁጣ ነበር። እናም ከለውጡ ማግስት እነዚህን በመልካም አስተዳደር እና ሌሎች የሕዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

በዚህም የሕግ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ አዳዲስ ሕጎችም ወጥተዋል። ተቋማት ነጻነታቸውን እንዲጎናጸፉ የሚያደርግና አቅም እንዲፈጥሩ የሚያስችላቸውን ዘርፈ ብዙ የሪፎርም ተግባራት ተከናውነዋል። የሥራ ከባቢን ሳቢና ለአገልግሎት ምቹ የሚያደርጉ ሥራዎችም ተሠሩ፡፡

ከዘመኑ ጋር መራመድ እንዲችሉና የሕዝብ ፍላጎትን ማርካት የሚያስችላቸውን የዲጂታል አሠራር ሥርዓት እንደየተቋማዊ ተጨባጭ ሁኔታቸው እውን እንዲያደርጉ ሆነው። ይሄም ከተለምዷዊ አካላዊ ምልልስና የወረቀት አሠራር የተላቀቀ ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲዘረጉ እድል ሰጠ፡፡

የመንግሥትን አገልግሎትና አስተዳደር ከማሻሻል አኳያ የተወሰዱ እነዚህ የሪፎርም ተግባራትም ከዓመት ዓመት ለውጥ እያሳዩ፣ ምሳሌ የሆኑ ተቋማትን መፍጠር የተቻለባቸውም ናቸው። ዛሬ ላይ በአገልግሎት ቅልጥፍናቸው ብቻ ሳይሆን፤ በቴክኖሎጂ ታግዘው ድካምና እንግልትን በሚቀንስ አሠራራቸው የሚገለጡ ምስጉን ተቋማት መፍጠር ተችሏል፡፡

በአንጻሩ፣ አንዳንዶች ካሉበት መንቀሳቀስ ተስኗቸው የሚንፏቀቁ፤ አንዳንዶችም በለውጥ ውስጥ እየተፍጨረጨሩ ያሉ፤ አንዳንዶቹም ተቋማዊ ገጽታቸው የተለወጠ ቢሆንም፤ የውስጥ አገልግሎት አሰጣጣቸው በ"ሲስተም የለም" ምክንያት የታጠረ የአገልግሎት አሠጣጥ ሂደትን የማስተጓጎልና የማጓተት፤ አለፍ ሲልም ላልተገባ ጥቅም ፍላጎታቸው ተገልጋዮችን አስገድዶ የማመቻቸት አዝማሚያዎች ውስጥ ያሉም አሉ፡፡

ከሰሞኑም በመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደር ጉዳዮች ላይ በማተኮር የመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም አመራር ዐቢይ ኮሚቴ ሦስተኛ መደበኛ ስብሰባውን ያካሄደ ሲሆን፤ በውይይቱም በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና በመጀመሪያ ዙር የተመረጡ ተቋማት ያከናወኗቸው የሪፎርም ሥራዎች ተገምግመዋል፡፡

የዐቢይ ኮሚቴውን መድረክ መነሻ አድርገውም፤ የሪፎርም አስተዳደራዊ ሥራዎች፣ ቀልጣፋና ተደራሽ የመንግሥት አገልግሎትና አስተዳደር ሥርዓትን መዘርጋት፣ የዲጂታል ሲቪል ሰርቪስ በመገንባት አገልግሎቶችንና ውሳኔዎችን ማቀላጠፍ ላይ ጥሩ ጅምሮች መኖራቸውን፤ በቀጣይም ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ላይም አቅጣጫ መቀመጣቸውን ነው የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ያሰፈሩት፡፡

በመሆኑም በዚህ መልኩ በአንድ በኩል የተለወጠ ተቋምና አሠራር፣ በሌላው ገጽ የለውጥ መስመሩ ላይ ያሉ ግን አሁንም በችግር ውስጥ የሚገለጡ የአገልግሎት ተቋማትና አሠራሮች መኖራቸው ከሕዝብ የተሰወረ አይደለም። እናም በአንድ በኩል የተገኘውን ውጤት አልቆ ማስቀጠል፤ በሌላ በኩል በአንዳንድ ቦታዎች የሚታዩ ችግሮችን እየለዩ ማረም ይገባል፡፡


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሀገር በቀል የትምህርት ሥርዓት ለህብረ ብሔራዊነት

**ህዝቂያስ ታደሰ (የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ መምህር)**

ሰውን ከተስፋና ምኞቱ የሚያደርሰው መሣሪያ ትምህርት ነው። ይኸ የሰውን ዕድል ለማሻሻል አቅም ያለውና ከእርሱም የሚገኘው ዕውቀት በብዙ ትግልና ድካም እንጂ በችሮታ አይደለም።

ለዚህ ሃሳብ አስረጂ ከሚሆኑት አንዱ የሃሳቤ ዓውደ-ዙሪያ የሆነው ኃይለ-ቃል ነው። "የቆሎ ተማሪ" ይሰኛል። ይህ ሥያሜ ከጽሑፉ ዓላማ ጋር ግንኙነት ስላለው ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙን ላስቀድምና በዚህ ኃይለ-ቃል ወደሚገለጠው ሃሳብ እመለሳለሁ።

የቆሎ ተማሪነት ከፍተኛ ትምህርትን፣ ሊቃውንትን፣ መምህራንን ፍለጋ ቤተሰቦቻቸውን፣ አካባቢያቸውን፣ ቀያቸውን ትተው ወደ ሩቅ ሀገር የሚዘምቱትን ይጠቅሳል። ጉዟቸው ከለመዱት፣ ከቤተሰባቸው፣ ከቀያቸው ወዲያ ወደማያውቁት፣ ወዳልለመዱት፣ ወደሚርቀው ነው። ይህ መሆኑ - አንድም ቤተሰቦቻቸው የልጆቹን እገዛ እና ድጋፍ በፈለጉ ቁጥር ሊፈጠር የሚችለውን የቤተሰቦቻቸውን ተደጋጋሚ ጉብኝት ለማስወገድ፣ በዚህም ሳቢያ ሊፈጠር የሚችለውን የትምህርት መስተጓጎል ለማስቀረት ሲሆን፤ አንድም ተማሪዎቹ ጥቃቅን ችግሮች በገጠሟቸው ወቅት ወደ ቤተሰባቸው ከመኮብለል ስለሚታደጋቸው፤ በሌላም ተማሪዎቹ ካደጉበት፣ ከለመዱት፣ ከቤተሰባቸው፣ ከቀያቸው በራቁ መጠን ዋናው ሃሳባቸውም ትኩረታቸውም በትምህርታቸው ላይ ብቻ እየሆነ ይሔዳል፤ ትምህርታቸውንም በሙሉ ልብ ለመከታተል ለመከወን ያስችላቸዋል ተብሎ በመታመኑ ነው።

ይሁን እንጂ፣ ተማሪዎቹ ይኼን መሰሉን ትምህርታዊ ጉዟቸውን የሚያደርጉት ራሳቸውን ለማቆየት የሚያስችል በቂ ስንቅ ሳይዙ ነው። ባህላዊ የትምህርት ተቋማቱም ቢሆኑ እንደዘመናችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለተማሪዎቻቸው ምግብ እና ሌሎች መሰል ድሎቶችን (facilities) አያቀርቡም። በዚህም ሳቢያ፣ ተማሪዎቹ በእነዚህ የትምህርት ቆይታ ጊዜያት የእለት እንጀራቸውን ፍለጋ አኮፋዳቸውን ይዘው መንደር ለመንደር በመዞር ይመፀወታሉ። ባጭሩ አኮፋዳቸውን ይዘው መቅፈፍ በመዞር ራሳቸውን ያከርማሉ፣ ትምህርታቸውንም ይቀጥላሉ። (መቅፈፍ - የተማሪ መንደር ለመንደር ዞሮ የመለመን ተግባርን ይገልጣል)።

እዚህ ላይ አስተውሎት እንዲኖረን ይገባል ብዬ የማስበው፣ በእነዚህ ባህላዊ ትምህርት ተቋማት ዙሪያ የሚኖረው የማህበረሰብ ክፍል ወይም የመንደሩ ነዋሪ ለእነዚህ በቀዬው ለሚመላለሱት ተማሪዎች የእለት እንጀራቸውን የመመጽወት የሞራል ግዴታ አለበት። ይሁን እንጂ፣ የተማሪዎቹ በአካባቢው ማህበረሰብ መንደር ውስጥ እየተዘዋወሩ የእለት እንጀራን የመፈለግ ልማድ ፋይዳው የተማሪዎቹን ሕይወት ከማቆየት ይሻገራል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት፣ ይህ የአካባቢውን ማህበረሰብ የመኀብኘት ልማድ በሂደት ከነዋሪው ጋር መግባባትን፤ ውሎ አድሮ ደግሞ ከማኅበረሰቡ ጋር በአመዛኙ ጠንካራ ማኅበራዊ ትስስር እና መስተጋብር መፈጠርን ማስቻሉ ነው።

ይህ ከራሳችን የሕሊና ፍሬዎች የበቀለ የባህላዊ ትምህርት ቤቶቻችን ተሞክሮ ትልቅ ጠቃሚ ትምህርት የሚሰጥ እና ምናልባትም ለትምህርት ችግራችን የታመነ መፍትሔ ሊያቀብል የሚችል ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ከዚህ አኳያ፣ እነዚህና መሰል ጠቃሚ ተሞክሮዎች በቅጡ ተለይተው፣ ተጠንተው፣ ተሻሽለው እና ዘምነው፣ ካስፈለገም ከዘመኑ የትምህርት ስነዘዴ ጋር ተጣምረው ወደ ዘመናዊው የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓታችን ቢካተቱ የሚበጅ ተግባር ነው የሚል እምነት አለኝ።

በዚህ ጽሑፌ ይህን ቤተ-ክርስቲያን መሠረት ያደረገው የሀገር በቀል የትምህርት ተቋማቶቻችን የጎልማሶች ትምህርት ሞዴል ጠቃሚ ተሞክሮ (መቅፈፍ የሚዞሩ የቆሎ ተማሪዎችን ተሞክሮ ይመለከታል) ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማቶቻችን የማሻገሩን እና የማጻመሩን የአጭር እና የረጅም ጊዜ ፋይዳ በጥቂቱ ለማሳየት እሞክራለሁ።

ይኸውም፣ በአጭር ጊዜ በተማሪዎቹ እና በአካባቢው ማህበረሰብ መካከል ጠንካራ ማህበራዊ ትስስር እና መስተጋብር ብሎም ዘላቂ ግንኙነትን ያጸናል። በረጅም ጊዜ ውጤቱም፣ ምናልባትም በእጅጉ የምንመኘውን በመላው የሀገሩ ሕዝብ መካከል የሕዝብ አንድነትን ያጸናልናል።

ስለዚህ፣ አንድነትን በተለያየ ደረጃ በማጎልበት ይህ ጠቃሚ ተሞክሮ ለትምህርት ችግራችን ምናልባትም ደግሞ ለሀገራችን አጠቃላይ ችግር መፍትሔ ሊጠቁም ይችላል የሚል እምነት አለኝ። ይህንም በተከታዮቹ ሶስት አርእስተ ጉዳዮች ለይተን እንመልከት።

### ለትምህርት ችግራችን የታመነ መፍትሔ ፍለጋ

አውሮፓውያን ከመካከለኛው ዘመን ለመላቀቅ ባደረጉት ተጋድሎ እርዳታ ፍለጋ፣ መሠረት ፍለጋ ወደገዛ ራሳቸው ምንጭ ነው የሔዱት። ወዳለፉት ነው ያማተሩት። ወደኋላ ሔደው በመፈለግ የግሪክን የፍልስፍና ሲስተሞች ዳግም ወደ ሕይወት ለማምጣት በመጣር ነው በዚያ ላይ የተመሰረተ አዲስ ሥልጣኔ የገነቡት። ይኸም የዳግም ልደት ዘመን (Rennaisance) በመባል የሚታወቀው የታሪክ ዘመን ነው። ባጭሩ የዘመናዊው የአውሮፓ ሥልጣኔ መንፈስ ከግሪክ ፈላስፎች የሠረፀ ነው ለማለት እንችላለን። ከዚህ ላይ፣ ማጎተማቸውን ከብዙ በጥቂቱ ብንጠቅስ በሳይንሱ ረገድ የአቶም ኃልዮት ላይ፣ በሥነ መንግሥት ረገድ በዲሞክራሲ ኃልዮት ላይ፣ በሕንጻ አቋቋም ላይ፣ በከዋክብት ምርመራ ላይ፣ በተግባረ-እድ ሙያ ላይ፣ በሥነ ፍጥረት ምርምር ላይ፣ በአእምሮ ምርመራ ላይ፣ ወዘተረፈ..... እናገኛለን።

ይህ የዘመናችን ትልቁ ሥልጣኔ ማለትም የአውሮፓ ሥልጣኔ ሥር ወይም ምንጭ ለያዝነው ሃሳብ ትልቅ አብነት፣ ትልቅ አስረጂ ነው። በእኔ እምነት፣ በዚህ ረገድ ወደ ውጭ ከመመልከት ይልቅ ከኛ በብዙ ልንወስድና ልናበቅለው የበቀለውም ሊያፈራልን የሚችል ነገር አለ።

ለምሳሌ ምን? ብሎ ማሳያ መጠየቅ በእጅጉ የተገባ ይሆናል፣ ብዬ አምናለሁ።

መልስ ከሚሆኑ ሃሳቦች አንደኛው ይህ ነው (ሌላኛውን በሚቀጥለው ጽሑፌ እመለስበታለሁ)።የእነዚህ የባህላዊ ትምህርታዊ ቤቶቻችን አንዱ ጠቃሚ ተሞክሮ እና ላለንበትም ዘመን ጠቃሚ ትምህርት የሚሰጥ ነው የምለው ተማሪዎቹ በዙሪያቸው ከሚኖረው የማህበረሰብ ክፍል ጋር ጥልቅ ማህበራዊ መስተጋብር የመፍጠርን ጥቅም በማጉላቱ ነው። ይህም ማለት፣ ከዘመናዊ የትምህርት ተቋማት አንጻር በአመዛኙ ጠንካራ የሆነ የተማሪ-ማህበረሰብ ትስስርን ማጎልበቱ ነው።

### የተማሪ-ማህበረሰብ ትስስርን ማጎልበት

ለምሳሌ ያደገበትን ቀዬ ለቆ አኮፋዳውን ሸክፎ ቅኔ ወይም ዜማ ለማጥናት ወደ ጎጃም ዋሸራ ማርያም የሚጓዝ ተማሪ ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ ተከታትሎ ለማጠናቀቅ ለዓመታት እዛው ይቆያል። በመሆኑም፣ ተማሪው ትምህርቱን እየተከታተለ በሚቆይባቸው በእነዚህ ዓመታት ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በጥልቅ ይቆራኛል።

ከዚህ በመነሣት፣ የሚከተለውን የተሰባጠረ የዩኒቨርሲቲ አመዳደብ ዘዴ ብንነድፍ የተማሪ-ማህበረሰብን ግንኙነትን የምናንጽበት ብልሀት

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ተንቀሳቃሽ የማስታወቂያ ሰሌዳ - የወጣቱ አዲስ ሃሳብ

ሰሚራ በርሀ

ወጣትነት ውስን ቦታ ፣ የተገደበ ከባቢን አይፈልግም። አዳዲስ ነገሮችን መሞከር፣ ማየት፣ ያለውን የወጣትነት ጉልበት መጠቀም እና የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት የሚገድበው ምንም ነገር አለመኖሩን ማረጋገጥ ይሻል። የተለያየ እሳቤና የሕይወት ልምድ በሚያስተናግድ ማህበረሰብ ውስጥ እድገቱን ያደረገ ሲሆን፣ ደግሞ ሕይወትን ሰፋ አድርጎ መወጠን የተለመደ ተግባር ይሆናል።

አብርሃም ሰመረ ይባላል። በአዕምሮው ያውጠነጠነውን ሃሳብ የሚጋራው ሰውም ሆነ የሚስማማ ትኩረት የሚሰጠው ሰው ስለመኖሩ ምንም ዓይነት መተማመኛ አልነበረውም። ነገር ግን በአእምሮው ያለውን ሃሳብ ወደ መሬት አውርዶ የሚኖረውን ውጤት ማወቅ ይሳካለት ይሆን ወይስ አይሳካለት የሚለውንም ማረጋገጥ ፈልጓል ።

አብርሃም፣ ተወልዶ ያደገው በደቡብ የሀገራችን ክፍል በወላይታ ሶዶ ከተማ ነው። ለወላጆቹ የመጨረሻ ልጅ ሲሆን፣ አብዛኞዎቹ እህትና ወንድሞቹ በትምህርት ውስጥ ያለፉ እና በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ናቸው። በወይላታ ሶዶ ከተማ እድገቱን ያደረገው አብርሃም፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ አዲስ አበባ ከተማ ወደምትገኘው እህቱ መጥቶ እሷን እያገዘ መማርን ምርጫው አደረገ። በትምህርቱ ጥሩ ደረጃ የነበረው አብርሃም፣ የራሱ የሆነ የሥራ መስክ አልያም ገቢ ማግኛ መንገድ መፈለግ ግን ከልጅነቱ ጀምሮ የሚሻው ጉዳይ ነበር ።

በመሆኑም አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ በራሷ የግል ንግድ ሥራ የተሰማራችውን እህቱን በማገዝ ትምህርቱን ሊማር ችሏል። ሕይወት በብዙ መንገድ ትመራናለች፤ በመሆኑም እድሎች ያለ ፈተና አልተገነቡም እና ማሳካት ለምንፈልገው ጉዳይ መስዋዕት ማድረግ ያለብን አሊያም መስጠት ያለብን ትኩረት አለ። አብርሃም የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በዚያው በአዲስ አበባ ትምህርቱን ለመከታተል ሲወስን በጎን ግን የትምህርት ቤት ክፍያውን እና ሌሎች ወጪዎቹን በራሱ መሸፈን ነበረበት። ‹‹የተለያዩ ሥራዎችን ሞክሬአለሁ እና ወጣት ሆኜ ወይም አድጌ ከቤተሰቦቼ ገንዘብ መቀበል ከባድ ነገር ነው። ›› ይላል። በታዳጊነት እድሜው ምንም እንኳን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ባያጠናቅቅም ራሱን መቻል እንዳለበትና የራሱን ኃላፊነቶች / ፍላጎቶች በራሱ መወጣት እንዳለበት አስቀድሞ ተረድቷል። በመሆኑም ማንኛውንም እውቀቱንም ሆነ ጉልበቱን ተጠቅሞ ሊሠራው የሚችለውን ሥራ ለመሥራት ራሱን አዘጋጅቷል። የኮሌጅ ትምህርቱን በማታ መርሀ ግብር በመማር የቀን ገቢ የሚያስገኝለትን ሥራ ደግሞ ጎን ለጎን መሥራት ነበረበት።

ወጣቱ አብርሃም፣ በተለምዶው “ሀይላንድ” የምንለውን የታሸገ ውሃ መያዣ ማምረቻ ድርጅት ውስጥ ሥራ አገኘ። ሥራውን የሚሠራበት አላማ ራሱን ለመቻል ሲሆን፣ በሥራ ራሱን ለማሳደግ የሚያደርገውንም ጉዞ የሚያሰምርለት የተሻለ ልምድ የሚፈጥርለት በመሆኑ ነው። ስለዚህም በጥቂቱ ሥራውን ለመላመድ ቢሞክርም በዚያ ፋብሪካ ውስጥ የነበረው የሥራ ሁኔታ እና አብርሃም የሚሠራው ሥራ ግን ከባድ እንደነበር ያስታውሳል። በመሆኑም አብርሃም፣ ሥራውን በመተው ሌላ የሥራ አማራጭ መፈለጉን ቀጠለ። ‹‹በተለያዩ ቦርሳዎች ላይ በተለያየ ዲዛይን ማስታወቂያዎች ይሠራሉ። እነሱን ሳይ ሳይክልን በመጠቀም በተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር ማስታወቂያዎችን ብሠራስ የሚል ሃሳብ መጣልኝ።›› ይላል።

“ባይክ ቢልቦርድ” የተለያዩ ማስታወቂያዎችን በተንቀሳቃሽ ሳይክል በማድረግ ተንቀሳቃሽ የማስታወቂያ ቦርድ ነው። አብርሃም ከልጅነቱ ጀምሮ ሳይክል በመንዳት ያሳለፈ ሲሆን፣ ሳይክል የልጅነት ትውስታው ውስጥ ቀድሞ ከሚያነሳቸው አንዱ ጉዳይ ነው። ታዲያ በማስታወቂያ ታሪክ ከምናያቸው የተለያዩ ድርጅቶች ሥራዎቻቸውን የተለየ መንገድ በመጠቀም ያስተዋውቃሉ ፤ የሚያሠሩት ይህ ማስታወቂያም ደንበኞችን እንዲስብላቸው እና ተደራሽነታቸውን በማሳደግ ገቢያቸውንና እውቅናቸውን ለመጨመር እንዲሁም ራሳቸውን ለማስተዋወቅ እና ድርጅቶቻቸውን ለማሳደግ ከሚጠቀሙበት መንገድ አንዱ ነው ማስታወቂያ ማሠራት። በሀገራችን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን የማስታወቂያ ሃሳብ በመጠቀም ራሱን ያስተዋወቀው አንድ የሳሙና አምራች በሀገሪቱ ቀደምት ጋዜጣ በሆነው አዕምሮ ጋዜጣ ላይ እንደነበር ይነገራል።



ወጣት አብርሃም ሰመረ፣




**ወጣቶቹ የሥራ ፍላጎት ያላቸው እና የራሳቸው ብስክሌት ያላቸውን በመቅጠር እና የራሱን የቢል ቦርድ ዲዛይን አውጥቶ በማስቀመጥ ከአንድ በላይ በመሆን በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንዲጓዙ ያደርጋል**

ታዲያ በጊዜ ሂደት ወቅቱ የፈጠራቸውን የማስተዋወቂያ መንገዶችን በመጠቀም ድርጅቶች ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ። ድርጅቶች ሥራቸውንና ራሳቸውን ለማስተዋወቅ የሚመርጡት ተቋም አብዛኛው ሊመለከተው አሊያም ትኩረት ሊሰጠው የሚችለው ፕላትፎርም ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አሁንም ድረስ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች፣ ራዲዮ ጣቢያዎች እንዲሁም የሕትመት የመገናኛ ብዙሃን ለማስታወቂያ የሚመረጡ ሲሆኑ፣ የማህበራዊ ትስስር ገጽ ደግሞ በአሁን ሰዓት በይበልጥ ለማስታወቂያ ተመራጭ እየሆነ መጥቷል። የተለያየ ድርጅት ያላቸው ተቋማት በማህበራዊ ትስስር ገጽ የራሳቸውን ገጽ በመክፈት ድርጅታቸውንና አገልግሎታቸውን ያስተዋውቃሉ። በእነዚህ ዘመንኛ የማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ የሚገኙ እና የራሳቸውን ስም በተለያየ መንገድ መገንባት የቻሉ ተጽዕኖ ፈጣሪዎችን በመጠቀም በራሳቸው ገጽ ላይ እንዲያስተዋውቁላቸው ግለሰቦችን ምርጫቸው ያደርጋሉ። አብርሃም የተለያዩ አዳዲስ እውቀቶችን ለማግኘት ማንበብ እና አዳዲስ መረጃዎችን መስማት አብዝቶ የሚወድ ነው ።

አብርሃም የብስክሌት ላይ ተንቀሳቃሽ ማስታወቂያ አዲስ ሃሳብ መሆኑን ሲረዳ እና የራሱን ጥናት ሲያደርግ ሃሳቡ በኢትዮጵያ አዲስና የማይታወቅ ሆነ እንጂ በሌላው ዓለም ራሱን የቻለ ኩባንያ ያለው የሥራ መስክ መሆኑን ተረዳ። በዚህም የራሱን ዲዛይን ካወጣ በኋላ ብስክሌት መግዣ እና የቢልቦርድ ሕትመት ማዘጋጃ የሚያስወጣውን ወጪ አስልቶ እህቱን አማከራት። ለሥራው መነሻ የሚሆን ገንዘብ እንድታበድረውም ጠየቃት ።

‹‹ለእህቴ ስነግራት ብዙም ሃሳቡ አልገባትም ነበር። ስለዚህ እንዳልከስር በመፍራት ያዋጣል ወይ? የሚለው ላይ ጥርጣሬ ነበራት።›› የሚለው አብርሃም፣ ያሰበውን ነገር በፍራቻ እና እከስራለሁ በሚል ምክንያት መተው አልፈለገም። በመሆኑም እህቱን አሳምኖ ገንዘቡን እንድትሰጠው እና ሥራውን ጀምሮ ባይሳካለት እንኳን ሌላ ሥራ ውስጥ ተቀጥሮ በመሥራት የተበደረውን ገንዘብ እንደሚመልስላት በማሳመን ሥራውን ጀመረ። ገና በሚጀምርበት ወቅትም የራሱን ብስክሌት ገዝቶ ከዚህ ቀደም በስፋት በየመንገዱ እና በየአደባባዮች ላይ በትልቁ ተሰቅለው የምናያቸውን የማስታወቂያ ቦርዶች አብርሃም በመጠኑ እና በራሱ ሃሳብ ዲዛይን በማድረግ በብስክሌት ላይ ምቹ እንዲሆኑ አድርጎ ሥራውን ጀመረ።

‹‹ስጀምረው የራሴን ስም እና አድራሻ አስቀምጬ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሳይክሌን ይዤ እየዞርኩ አስተዋወቅኩ።›› ሲል ይናገራል። አብርሃም፣ ሥራው አዲስ የፈጠራ ሃሳብ በመሆኑ በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተማዎች ላይ በመዘዋወር ራሱን ካስተዋወቀ በኋላ የመጀመሪያ የማስታወቂያ ሥራው በይበልጥ ራሱን እንዲያስተዋውቅ አደረገው ።

የማስታወቂያ ሥራው ለሌሎች ሰዎች ይበልጥ ግልጽ በመሆን አዳዲስ ደንበኞችን እንዲስብለት በማሰብ በምስል ከሚተዋወቀው ቢልቦርድ በተጨማሪ የድምጽ ማስታወቂያንም በብክስሌቱ ላይ አብሮ ይዞ ይጓዛል። አብርሃም፣ ሌሎች ማስታወቂያዎችን በሚሠራበት ወቅት ለደንበኞቹ ታማኝነትን ለመፍጠር ማስታወቂያዎቹን ይዞ በሚጓዝበት ወቅት የሚንቀሳቀስበትን አድራሻ በቴሌግራም እና የጎግል ማፕ መጠቆሚያ በማጋራት ደንበኞች ማስታወቂያቸው በየት አካባቢ እንዳለ በቀጥታ ማየት እንዲችሉ ያደርጋል ።

አብርሃም፣ አሁን ላይ የሚሠራው ይህ የሳይክል ማስታወቂያ ሥራ እውቅና እና ተወዳጅነትን እያገኘለት ሲሆን፣ ሰዎች በተለያየ መንገድ አብርሃምን አግኝተው ድርጅታቸውን በዚህ ተንቀሳቃሽ የማስታወቂያ ቢልቦርድ ላይ ማስተዋወቅ የሚፈልጉ ደንበኞችም በርከት ማለት ጀምረዋል።

የማስታወቂያ ሥራ እንዲሠራላቸው ከተስማሙ በኋላ ማስታወቂያው የሚንቀሳቀስበት ሰፈር በደንበኞቹ ምርጫ ያደርጋል። ‹‹የተለያዩ ቦታዎች ላይ እንዘዋወራለን፤ ምርቱን በትክክል ሊገዙት አሊያም ሊጠቀሙት ይችላሉ የምንላቸው ደንበኞች የሚገኙበት ቦታ በመምረጥ ወይም ደግሞ ደንበኞቻችን በፈለጉበት አካባቢ እንቀሳቀሳለን።›› በማለት ያስረዳል። አብርሃም ማስታወቂያዎቹን ለመሥራት ሰዎች የሚበዙባቸው ቦታዎች ላይ የሥራ መግቢያ እና መውጫ ሰዓትን ይጠቀማል። ምርቶቻቸውን ማስተዋወቅ ለሚፈልጉ ደንበኞች የሚያስከፍልበት እና የሚሠራበትን መንገድ በጥቅል መልክ በማድረግ አቅርቧል። ‹‹ማስታወቂያ ለሚፈልጉ ደንበኞቻችን የሳምንት፣ የወር የሚሉ ጥቅሎች አሉን። በዚህ መሠረት ከሠራን በኋላ የውላችን ጊዜ ሲያልቅ ማስታወቂያ ባነሩን ለእነርሱ እንሰጣቸዋለን። ›› ይላል።

አብርሃም፣ ሥራውን በይበልጥ ማህበራዊ ትስስር ገጽን በመጠቀም የሚያስተዋወቅ ሲሆን፣ በአሁን ሰዓት የእንጨት ሥራ የፈርኒቸር ውጤት አምራቾች፣ የውበት ሳሎኖች፣ የፎቶ ባለሙያዎች ሥራዎቻቸውን /ድርጅታቸውን በአብርሃም ማስታወቂያ ላይ ያስተዋውቃሉ። አሁን ላይ በከተማችን አዲስ አበባ የብስክሌት መንገዶች የተሠሩ ሲሆን፣ የብስክሌት መሽከርከሪያ መንገዶች ባልተሠሩባቸው ቦታዎች ላይ በቀስታ በማሽከርከር ሰዎች መረጃውን እንዲዩት ያደርጋል።

‹‹መጀመሪያ ስጀምረው ተቀይባነት ይኖረዋል ብዬ አላሰብኩም ነበር። ነገር ግን ሰዎች ቶሎ ተቀብለውታል፤ ያነቡታል፤ በድምጽም ደግሞ ይሰሙታል። ያዩትን ነገር ሲሞክሩም ተመልክቻለሁ።›› ሲል በቶሎ ያገኘውን ተቀይባነት ይገልጻል። ወጣቱ አብርሃም፣ አሁን ላይ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሲሆን፣ በዚህ ሥራው አብረውት የሚሠሩ ሌሎች ብስክሌት ያላቸው ስድስት ወጣቶችን በስሩ አድርጎ እየሠራ ይገኛል።

ወጣቶቹ የሥራ ፍላጎት ያላቸው እና የራሳቸው ብስክሌት ያላቸውን በመቅጠር እና የራሱን የቢል ቦርድ ዲዛይን አውጥቶ በማስቀሠመጥ ከአንድ በላይ በመሆን በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንዲጓዙ ያደርጋል። ወጣቱ አብርሃምም ብስክሌቱን ይዞ ሥራውን ከማስተዋወቅ አገልግሎቱን ከሚፈልጉ ደንበኞቹ ጋር በመወያየት በማሳመን ሥራውን በማስተዋወቅ ተጨማሪ ደንበኞችን ለማምጣት የገበያ ልማት ሥራውን ያከናውናል።

ራሱን ለማሻሻል እና የራሱን ገቢ ለማምጣት ያለመውን ሃሳብ ወደ መሬት በማውረድ መልካም የሚባል መንገድ ላይ ይገኛል። ‹‹በሥራ ላይ አንድ የማምንበት ነገር ቢኖር ያመንበትን ነገር ፈርተን መተው እንደሌለብን ነው፤ መሞከር እና የሚኖረውን ውጤት ማየት ወሳኝ ነው። ሞክረነው ባይሳካልንም እንማርበታለን፤ ወደ ስኬት የምንቀርበው ያመነውን ነገር በመሞከራችን ነው ብዬ አስባለሁ። ›› ሲል ለሌሎች ታዳጊዎች እና ወጣቶች ምክሩን ያጋራል።

# የምድር በረከት

# የማዕድን ዘርፉ አበረታች ውጤቶች

**ወርቅነሽ ደምሰው**



የማዕድን ዘርፍ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትኩረት ከተሰጣቸው አምስት ዘርፎች መካከል አንዱ ነው። ዘርፉ ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር ለበርካታ ዜጎች ሰፊ የሥራ እድል የሚፈጥር ስለሆነ ትኩረት ተሰጥቶት በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዘርፉ በተከናወኑ ተግባሮች መነቃቃት እያሳየ መምጣቱንና አበረታች ለውጦች እየተመዘገቡ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

በተያዘው 2017 በጀት ዓመትም መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ተግባራዊ ማድረጉ እና በወርቅ መግዣ ዋጋ ላይ የተደረገው የማበረታቻ ሥርዓት፣ ኮንትሮባንድን በመቀነስ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከቱ ይገለጻል። ይህን ተከትሎ ባለፉት ስድስት ወራት በማዕድን ዘርፉ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ ስለመሆናቸውም የማዕድን ሚኒስቴር መረጃ ያሳያል።

መረጃ እንዳመላከተው፤ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተለያዩ ማዕድናትን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከ376 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ታቅዶ፤ አንድ ነጥብ 047 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ተችሏል።

ለውጭ ገበያ ለመላክ ከታቀደው የማዕድናት ዓይነቶች መካከል 180 ቶን ታንታለም፣ ስድስት ቶን ጥሬ እና ግማሽ ቶን እሴት የተጨመረበት ኦፓል፣ ከ14 ቶን በላይ የጌጣጌጥ ማዕድናት፣ አንድ ሺህ 400 ሜትር ኪዩብ እምነበረድ፣ ስድስት ሺህ ቶን ሊትየም ኦር እና 18 ሺህ 750 ቶን የኢንዱስትሪ ማዕድናት ይጠቀሳሉ ።

በግማሽ ዓመቱም 16ነጥብ886 ቶን ወርቅ፣ 105ነጥብ19 ቶን ታንታለም ኦር፣ 2071 ነጥብ48 ቶን ሊትየም ኦር፣ 5ነጥብ66 ቶን ጥሬ እና እሴት የተጨመረበት ኦፓል ፣ 0ነጥብ254 ቶን ጌጣጌጥ /ከኦፓል ውጪ/፣ 10357 ነጥብ35 ቶን የኢንዱስትሪ ማዕድናት እና 3014 ቶን ሶዲየም ብሮማይድ ለውጭ ገበያ መላኩ ተገልጿል።

ከወርቅ ውጭ ባሉ የኢንዱስትሪና ጌጣጌጥ ማዕድናት 22 ነጥብ 46 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እንደነበር መረጃው ጠቁሞ፤ 16 ነጥብ 44 ሚሊዮን ዶላር በማግኘትም የእቅዱን 73 በመቶ ማሳካት ተችሏል ብሏል። የጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ሂደት እንዲገቡ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጋር የጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ሊከተል ስለሚገባው አካሄድ ሰነድ መዘጋጀቱም ተጠቁሟል።

በስድስት ወራቱ የወርቅ ምርት በኩባንያዎች ሁለት ነጥብ 55 ቶን እና በባሕላዊ ማዕድን አምራቾች አንድ ነጥብ ስምንት ቶን፤ በአጠቃላይ አራት ነጥብ 35 ቶን ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ በማቅረብ ከ354 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ታቅዶ ነበር። በአፈጻጸሙም በኩባንያ አማካኝነት አንድ ነጥብ 392 ቶን፤ በባሕላዊ 15 ነጥብ 493 ቶን ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ ተችሏል። በአጠቃላይ በስድስት ወራቱ 16 ነጥብ 886 ቶን ወርቅ በማቅረብ፤ የታኅሣሥ ወር ምንዛሪን ሳይጨምር አንድ ነጥብ ዜሮ ሦስት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል።

ለአፈጻጸሙ ከፍ ማለት ዋናው ምክንያት እንደ ሀገር የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተጠቅሷል። ይህም በወርቅ እቅድ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያበረከተ ነው። በወርቅ መግዣ ላይ የተደረገው የማበረታቻ ሥርዓት ተግባራዊ በመደረጉ የሚመረተው ወርቅ የኮንትሮባንድ ተጋላጭነት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አድርጎታል።

ይህም በባሕላዊ መንገድ እና በኩባንያዎች ተመርቶ ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው የወርቅ መጠን፤ በስድስት ወራት ለማቅረብ ከተቀመጠው እቅድ አንጻር ከ366 በመቶ በላይ እንዲሆን አድርጎታል። በወርቅ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ የታኅሣሥ ወር ምንዛሪን ሳይጨምር፤ አንድ ነጥብ ዜሮ ሦስት ቢሊዮን ዶላር የተገኘ ሲሆን፤ የተገኘው ገቢ ከእቅድ አንጻር ሲታይ 388 በመቶ መጨመሩን አመላክቷል።

በወርቅ ምርትና ግብይት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ከመፍታት አንጻር ለኩምሩክ የወርቅ አምራች ኩባንያ ቅድመ ምርት ሥራዎች ላይ ችግር የሆኑበትን ጉዳዮች በመለየት ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጋር በመሆን ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ሥራዎች ተሠርተዋል።

**በአጠቃላይ በስድስት ወራቱ 16 ነጥብ 886 ቶን ወርቅ በማቅረብ፤ የታኅሣሥ ወር ምንዛሪን ሳይጨምር አንድ ነጥብ ዜሮ ሦስት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል**

በተጨማሪም በትግራይ እና በጋምቤላ ክልሎች የወርቅ ኩባንያዎች አሁናዊ ሁኔታ የመቃኘት ሥራ የተሠራ ሲሆን፤ በአራት ወርቅ አምራች ክልሎች በተመረጡ ወረዳዎች የባሕላዊ ወርቅ አምራቾችን እና ክልሎችን በመስክ የመደገፍ ሥራ ተሠርቷል።

ከውጭ የሚመጡ የማዕድን ውጤቶችና ጥሬ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ ምርት ከመተካትና የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦትን ከማሳደግ አኳያም የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ እየተመረተ ስለመሆኑ በመረጃው ተጠቁሟል። በስድስት ወራቱ አንድ ነጥብ 098 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል ለሀገር ውስጥ ተጠቃሚ ፋብሪካዎች ለማቅረብ ታቅዶ፤ 0ነጥብ 409 ሚሊዮን ቶን ማቅረብ ተችሏል።

አፈጻጸሙ የዕቅዱ 37ነጥብ 2 በመቶ ነው። ዝቅተኛ ለመሆኑ በምክንያትነት ከተጠቀሱት ተግዳሮቶች መካከል የድንጋይ ከሰል ክምችት መጠን ዝርዝር ጥናት/Exploration/ በጥራት ያለመኖር፤ ወጥ የሆነ የድንጋይ ከሰል ሴክተር የሚመራበት የሕግ ማሕቀፍ አለመኖር፤ አምራቾች በዘርፉ በቂ ዕውቀት የሌላቸው በመሆኑ በየአካባቢው ጥራት የሌለው ምርት እንዲመረትና ብዙ የድንጋይ ከሰል ሀብት እንዲባክን ምክንያት መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል። ፍላጎትን ያማከለ ምርት እየተመረተ አለመሆኑም የሌላቸው ተግዳሮት ተብሏል። በአንዳንድ ቦታዎች ድንጋይ ከሰል በቆይታ ምክንያት የመቃጠል ሁኔታ ያጋጠመ መሆኑ ተጠቁሟል።

የገበያ ትስስር ችግር መኖሩም ሌላው ተግዳሮት ነው። በቤኒሻንጉል፣ ደቡብ ምዕራብ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች በድንጋይ ከሰል አምራቾች እና በማጠቢያ ፋብሪካዎች የዳሰሳ ጥናት የተገኘው ውጤት የዘረፉን ተግዳሮቶች አመላክቷል።

የማዕድን ኢንዱስትሪ ምርት ማሳደግ አኳያ የሲሚንቶ ምርት ማሳደግ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸው ተጠቁሟል። እንደ መረጃው በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት አምስት ነጥብ 81 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ለማምረት ታቅዶ፤ ሶስት ነጥብ 86 ሚሊዮን ቶን ለማምረት ተችሏል።

የተመረተው የሲሚንቶ መጠን ከእቅድ አንጻር 66 ነጥብ 44 በመቶ ሲሆን፤ ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ10 በመቶ ብልጫ የታየበት ነው።

የሀገሪቱን የሲሚንቶ ፍላጎት ለማሟላት አዳዲስ ሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ወደ ሥራ በማስገባት የምርት አቅርቦትን የበለጠ ለማሻሻል የሚያስችሉ ሰፋፊ ሥራዎች መሠራታቸውን መረጃው አመልክቶ፣ ለዚህም የለሚ ብሔራዊ ሲሚንቶ ፋብሪካ ወደ ማምረት ሥራ እንዲገባ መደረጉን በአብነት ጠቅሷል።

መረጃው እንደጠቆመው፤ ሌላው በብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የተከናወነው ተግባር። በኢንዱስትሪዎች 0ነጥብ35 ሚሊዮን ቶን ብረት ለማምረት ታቅዶ፣ 0 ነጥብ 209 ሚሊዮን ቶን ነው ማምረት የተቻለው። አፈፃፀሙ 59 ነጥብ 7 በመቶ ሲሆን ዝቅ ያለበት ምክንያት በጥሬ ዕቃ እጥረት የተነሳ የብረት አምራች ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ማምረት ባለመቻላቸው ነው። ይህ አፈጻጸም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ46 በመቶ ብልጫ ያለው መሆኑን ያሳያል።

በተጨማሪም መሠረታዊ ብረታ ብረት አምራች ኢንዱስትሪዎች ላይ ነባራዊ ሁኔታ ጥናት እና የአርማታ ብረት ማምረቻ ወጪ እና መሸጫ ዋጋ ትመና ሥራ በተመለከተ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር መሠራቱም ተመላክቷል።

በሀገር ውስጥ የግብዓት አቅርቦት እጥረት፤ በተለያዩ ደረጃዎች ቅንጅት ማጣት፤ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት ማሟላት የሚችል ብቁ የሰው ኃይል አለመኖር (የክህሎት ክፍተት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር) እና ሕገ ወጥ ንግድ እና ደረጃውን ያልጠበቀ ምርት ብረትን በማምረት ረገድ ካጋጠሙ ተግዳሮቶች መካከል እንደሚጠቀሱም በመረጃው ተጠቁሟል።

መረጃው እንደጠቆመው፤ በማዕድን ልማት ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ አቅም እና ልምድ ያላቸውን ባለሀብቶች ፈቃድ በመስጠት የዘርፉን ኢንቨስትመንት ማሳደግ እንዲሁም በዘርፉ ተሰማርተው ለሚገኙ ባለሀብቶችን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ወደ ልማትና ምርት ሥራዎች እንዲገቡ በማድረግ ዘርፉ ለኢኮኖሚው አስተዋጽኦ እንዲያበረክት በማስቻል ረገድ በርካታ ተግባሮች ተከናውነዋል።

በዚህም ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች 10 (ሦስት የምርት፣ አንድ የፕሮሰሲንግና ስድስት የፍለጋ) እና ለውጭ ባለሀብቶች ስድስት (ሁለት የምርት፣ አንድ የፕሮሰሲንግና ሦስት የፍለጋ) በአጠቃላይ ለ16 ባለሀብቶች የፍለጋ፣ ምርትና ፕሮሰሲንግ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ፤ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች 13 የፍለጋና ሁለት የፕሮሰሲንግ እንዲሁም ለውጭ ባለሀብቶች አንድ የፍለጋ አጠቃላይ በድምሩ 16 ባለሀብቶች ፍቃድ መሰጠቱ ተመላክቷል። በተጨማሪም 50 የግብይት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ፤ በቁጥር 160 የግብይት የብቃት ማረጋገጫ መስጠቱ ተገልጿል።

በእነዚህ አዲስ በሚሰጡ የማዕድን ፍለጋና ልማት ፍቃድ 144 ሚሊዮን ብር የኢንቨስትመንት ካፒታል ለማስመዝገብ ታቅዶ ከፍተኛ አፈፃፀም መመዝገቡም ተጠቁሟል። ለአፈጻጸሙ የላቀ መሆንም ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ካፒታል ያስመዘገቡ ኩባንያዎች ፍቃድ መውሰዳቸው መሆኑ ተጠቁሟል። 20 በማዕድን ዘርፍ የምርመራና የምርት ፍቃዶችን፣ 61 የግብይት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትና 15 በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ሰርተፊኬት ዕድሳት መደረጉን ተመላክቷል።

በ48 የማዕድን ምርትና ምርመራ ፍቃድ የወሰዱ ኩባንያዎች ላይ በመስክ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ፤ በ26 ፍቃዶች (የዕቅዱን 54 በመቶ) በመስክ ክትትል ማድረግ ተችሏል። በክልል ለባሕላዊ አምራች ኢንተርፕራይዞችን 2500 ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ 3857 ፍቃድ ተሰጥቷል።

ሌላው በጂኦተርማል ዘርፍ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማሳደግ ከተሠሩ ሥራዎች መካከል የሁለት የጂኦተርማል ጉድጓድ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ዕድሳት ለማከናወን ታቅዶ ፤ የሁለት ፒኤልሲዎች ጂኦተርማል የፍቃድ ዕድሳት እና የምርመራ ፍቃዶች ዕድሳት መስጠት ተችሏል።

ለሌሎች ሁለት የጂኦተርማል የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ የይሁንታ ፍቃድ የመስጠት፣ ለሁለት የጂኦተርማል ሥራ ፍቃዶች ላይ የመስክ ክትትል፣ 11 የጂኦተርማል ምርመራ አፈጻጸም ሪፖርትና የሥራ ፕሮግራም በመገምገም የጂኦተርማል ኩባንያዎች እንቅስቃሴ ለመከታታል መቻሉ ተመላክቷል።

ከማዕድን ዘርፉ የሚገኘውን የሀገር ውስጥ ገቢ ከማሳደግ ረገድም ባለፉት ስድስት ወራት ከማዕድን ምርት 200 ሚሊዮን ብር የሮያሊቲ ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ፤ 162ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል።

ከፍቃድ ማውጫ፣ ከመመዝገቢያ፣ ከማደሻና ከሞያ ብቃት ክፍያ 0ነጥብ932 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ፤ 0ነጥብ696 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ከክልሎች የማዕድን ሥራዎች ልዩ ልዩ ገቢ 434ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ በታቀደው መሠረት ሲሠራ ቆይቷል።

የማዕድን ዘርፉ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል የሚፈጥር እንደመሆኑ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት በማዕድን ዘርፍ ኩባንያዎችና ኢንዱስትሪዎች ለ1,000 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፤ 522 (አዲስ በተሰጡ የማዕድን ፍቃዶች 341 እንዲሁም በጂኦተርማል 181) ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ተችሏል።

በባሕላዊ አምራች ኢንተርፕራይዞች ለ111 ሺህ 512 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፤ ለ102 ሺህ 33 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን አመልክቶ፤ ከዚህ ውስጥ ለአንድ ሺህ 18 ዜጎች የተፈጠረው የሥራ ዕድል በኦፓል ማዕድን ላይ እሴት መጨመሩ የማዕድን ሚኒስቴር መረጃ ያሳያል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ‹‹ደርሰሀል››

ሀብታሙ ባንታየሁ

ምስጋና ለጥምቀት ሎሚ ይግባና ፡-
"ጎንደር አባ ጃሌው ከግንቡ ደርሼ፣
ያለ እድል አይሆንም መጣሁ
ተመልሼ። "

ብሎ ከመዝፈን አድኖኛል። እኔና መክሊት ትውውቃችን የሚጀምረው ጥምቀትን በጎንደር ለማክበር በተገኘንበት አጋጣሚ ነበር። በውብቷ ተማርኬ የወረወርኩት ሎሚ የሷን ደረት ስቶ የአባቷ ፊት ላይ አረፈ። የአባት ቁጣ አስደንብሮኝ ለጊዜው ብሸሽም በሶስተኛው ቀን የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት አጅበን ወደ ቤቱ ስንሸኝ አገኘኋት። ባለፈው ድርጊቴ ተሳስቀን አድራሻ በመለዋወጥ አዲስ አበባ ልንገናኝ ቀጠሮ አደረግን። እህል ውሃ ሲያገጣጥም እንዲህ አይደል?

መክሊት በምትሰራበት የገቢዎች ቢሮ የኦዲት ባለሙያ ነች። ከሥራ የተረፈ ጊዜዋን እኔ ጋር ታሳልፋለች። አሮማይንና ፍቅር እስከ መቃብርን አብዝቼ እንደምወድ ስለምታውቅ " ፊያሜታን ልሁንልህ ወይስ ሰብለወንጌልን?" ትለኛለች ጨዋታ መጀመር ሲከጅላት። ፊያሜታን ብትሆኚ ወጪ ወራጁ "ዓመት ዓመት ድገመኝ" እያለ የሚጠረጥረው እንደ መንገድ ዳር የሽምብራ እሸት ጠርጣሪሽ ይበዛና ልቤን ሳታገኚው በከንፈር ትቀሪብኛለሽ። ሰብለ ወንጌልን ብትሆኚ ደግሞ እርግዝናዋ አስገድዷት የተስካር ፍትፍት እንዳማራት ነገር ግን የንጉስ ሚስትነቷ አንቆ ይዞ አላስበላ ብሏት አመል እንደነሳት ሁሉ እኔ እና አንቺም አጥር እናበጅና የጥበበ ወርቅዬን "እየተያየን ተለያየን" ለማንጎራጎር እንገደዳለን። እና ስለዚህ ወርቅ ሆነሽ እንደጠበቅሽኝ ወርቅ ሆኜ መጥቻለሁና እራሳችንን ብንሆን አይሻልም? ብዬ ሳቅፋት የሀዲስ አለማየሁንና የበአሉ ግርማን ዓለም ትተን የፍቅር አምላክ ባርኮ በሰጠን ዓለም ካጽናፍ እስከ አጽናፍ ሾርንበት።

እጅ ለእጅ ተያይዘን የተጓዝንባቸው ጎዳናዎች አበባ ጎፈሬአቸውን ነስንሰው የማዲንጎ አፈወርቅን "ጎዳናውን" ሙዚቃ እያዜሙ "ከአይን ያውጣችሁ" ብለው ሲመርቁን መክሊት የምትሆነው ይጠፋታል። ፍቅሯ በህልሜ አንጎራጉሬው ስነቃ እንደጠፋብኝ ዜማ ስስታም ያደርጋል። ይህን ጊዜ

እልልታው ይደምቃል ሙሽራ ሲገባ፣
ሀደ አካለ ሆይኑ ንቦች ከአበባ።

እልና የትዳር ፍላጎቷን በመላ ቀስቅሼ የሠርጋችንን ቀን ቆርጣ እንድትነግረኝ ጠይቃታለሁ። እሷም "ሀብት ሳንፈጥር?" የሚል መልስ ትሰጠኛለች። በአንደኛው የእረፍት ቀናችን ለጉብኝት በሄድንበት ላሊበላ ክፍል ይዘን ሰውነቷን ልትለቃለቅ መታጠቢያ ቤት እንደገባች በስልኳ ያስቀረቻቸውን ፎቶዎቻችንን በትዝታ ስቃኝ ምሽታችንን የሚረብሽ የጹሑፍ መልዕክት ሲንቀለቀል መጣ። ጹሑፉን ካየሁት በኋላ ጎጆ እንድንወጣ ስወተውታት "ሀብት ሳንፈጥር?" ማለቷ ለዚህ ይሆን እንዴ? ስል ጠረጠርኩ። ምን አልባት ሙያዋን ለሕገ ወጥ የሀብት ማካበቻ ተጠቅማበት ይሆን? የሚል ስጋት ያዘለ ሀሳብ መንፈሴን አወከው። ከሻወር ቤት ስትመለስ ፈክቶ የዋለው ፊቴ ዳምኖ ደረሰችበት። ሁኔታዬ ግር ቢላት የቁም መስታወቱ ውስጥ ተደበቀች።

የዘመን ቅሪት ነው እንዴት ያለ ጉድ፣
ቢያምጡት ቢያምጡት የማይወለድ።

ስጠራት የግዷን ዞራ ስታየኝ ተኩሰው የሳቱት ነብር ሆኛለሁ። ያጎረስኩትን ሽጉጥ ግንባሯ ላይ ደግኜ እዋሻለሁ ብትይ በነፍስሽ ፈረድሽ... ይህ ጽሑፍ ምንድነው? አልኳት ሞባይሏን እያቀበልኳት። እጇ እየተንቀጠቀጠ ካነበበችው በኋላ አንደበቷ ተሳስሮ ምላሷን ዋጠች። ያረበበውን ዝምታ ገፍፌ እስከዚች ደቂቃ ድረስ አንቺነትሽን አላገኘሁትም ነበር፤ እስኪ አሁን እንኳን እንዳውቅሽ ፍቀጅልኝ? አልኳት ለመረጋጋት እየሞከርኩ። "አባትህ ናቸው" ብላ ንግግሯን ስትጀምር መራራው እውነት እንደ ኮሶ እየታገለኝ ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ሆነብኝ። "የመጣባቸው ግብር ከገመቱት በላይ ሆኖ መክፈል ስላልፈለጉ ፍቅራችንን ማሸነፊያ ሲያደርጉት እኔም ከማጣህ ብዬ ሙያዬን በመጠቀም ተባበርኳቸው" አለች እንባ የቋጠሩ አይኖቿን ባይበሉባዋ እንደ እንጭጭ በቆሎ እያርመጠመጠች። ግብር በመሰወር የሀገሬን ሀቅ አሳጥተሽ በወንጀል የወዛው ፍቅራችን በለጠብሽ? ዮሴፍ ድንግል ማርያምን እንዲጠብቃት መታዘዙን ምልክት የሆነው በትሩ እንደ ሎሚ ዛፍ መለምለሟ ነበር፤ አንቺ ግን ፀሐይ እንዳጠወለገው ጎመን ኩምሽሽ አደረግሺኝ።

በጉብኝት ወቅት የተዋወቅናቸው በእድሜአቸው ጠና ያሉ ሰውዬ ክፍል የያዙት ከጎናችን ነበር። ጩኸታችን በርክቶ ሲሰሙ መጡ፣ በራችንን አልፈው ሲገቡ ሽጉጥ ይዤ ተመለከቱ። መላ ሰውነታቸውን አማትበው እያዳፉ ካስወጡኝ በኋላ ቁና ሙሉ እየተነፈሱ ምን እንደሆንን ጠየቁኝ። የሷን እና የአባቴን ሀጥያት ነግሬ በሁለት ቢላ መታረዴን ሳዋያቸው "የእኔ ልጅ... ነብዩ ሕዝቅኤል የፈረሰችውን የአባቱን ከተማ እየሩሳሌምን የገነባት በ25 ዓመቱ ነው፤ አንተም ወጣትነትህን ለሀገርህና ለፈጣሪህ ከሰጠህ እንደ ሶምሶን በደሊላ ፍቅር ከደረሰበት ከመንፈስ ቅዱስ ሽሽት ከህሊና ውግዘት ትድናለህ" አሉና ትንፋሽ ወስደው ልብን የሚያሞቅና ለሞራል ስንቅ የሚሆን ሌላ ታሪክ አስከተሉ።

"ከርከሮና ጅብ "እኔ ነኝ ቆንጆ" በሚል ተወራርደው ለዳኝነቱ ከጦጣ ዘንድ ቢሄዱ ወደ ሰው መራቻቸው። ከገበሬው ዘንድ እንደቀረቡ አያ ጅቦ "ለእኔ ባትፈርድ ከታዛ የምታስራት አህያ አለቀላት" ሲል አስጠነቀቀው። ከርከሮም በተራው "እኔን ባትል የዘራኸው በቆሎ ወዮለት" በማለት አስፈራራው። ገበሬውም ሳይደናገጥ በእርጋታ ሲያስብ ቆየና ማለፊያ ብልሀት ዘየደ። "ፍርድ እንድሰጥ የምትሹ ከሆነ ስጠራችሁ በየተራ ትገባላችሁ" ብሎ ችሎቱን ሰየመ። ከዚያም አያ ጅቦን አስቀድሞ በጆሮው "አንተ ነህ ቆንጆ" ሲለው እየፈነደቀ ሄደ፤ ከርከሮንም እንዲሁ ሲለው ደስ ብሎት በፊናው ተጓዘ። እናም የእኔ ልጅ... ሞፈር ተይዞ ወደ ኋላ አይሳብምና "የፊት የፊቱን እንዲል ጓያ ነቃይ" የሀገርህን እንባ ለማበስ ስለደረስክ መንገድህ ይጠራ ዘንድ አስተውል" እያሉ ሲገስጹኝ፣ ሀገሬን የእጇን ከሚነጥቋት ቀማኞች ልጠብቃትና በአጉራ ዘለሎች ባድማዋ እንዳይደፈር ብረት መዝጊያ እሆናት ዘንድ ናፈቀኝ።

# ዓለም አቀፍ

## በሎስ አንጀለስ እንደገና የተቀሰቀሰው ሰደድ እሳት እየተስፋፋ ነው

በሎስ አንጀለስ እንደገና የተቀሰቀሰው አዲሱ ሰደድ እሳት በፍጥነት እየተስፋፋ መሆኑ ተገለጸ። በፍጥነት እየተስፋፋ ያለውን አዲስ ሰደድ እሳት በመፍራት በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከሎስ አንጀለስ እየሸሹ ይገኛሉ ተብሏል።

ሎስ አንጀለስ ባለፉት ሳምንታት በታሪክ ያልታየ ሰደድ እሳት ገጥሟታል። አዲሱ ሰደድ እሳት ጥር 14 ቀን 2017 ዓ.ም ከከተማዋ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ነው የተነሳው።በተራራማው ካስቲክ ወንዝ አካባቢ የተነሳው ሰደድ እሳት በመኖሪያና ትምህርት ቤቶች አቅራቢያ ተስፋፍቷል ነው የተባለው።

ከቁጥጥር የወጣው ሰደድ እሳት ከ3 ሺህ 723 ሄክታር በላይ ተስፋፍቷል። በነፋስና በደረቅ ደን ምክንያት የሚስፋፋበት ፍጥነት ጨምሯል። ቤትም ይሁን የንግድ ቦታ በሰደድ እሳቱ ባይጎዳም ወደ 31,000 ነዋሪዎች ለመሸሽ ተገደዋል። ከአሜሪካ ምሥራቃዊ ክፍል ወደ ሜክሲኮና ካናዳ የሚወስደው አውራ ጎዳና ተዘግቷል።




አዲሱ ሰደድ እሳት ወደ ሰሜናዊ አቅጣጫ እየተስፋፋ ሲሆን፣ ባለፉት ሳምንታት በተነሳው ሰደድ እሳት ሳቢያ እነዚህ አካባቢዎች አሁንም እየተቃጠሉ ነው።በሳን ዲየጎና አሸንሳይድ ሁለት ሌሎች ሰደድ እሳቶች መነሳታቸውም ተገልጿል። የእሳት አደጋ ሠራተኞች እሳቶቹን መቆጣጠር ችለው ነዋሪዎችንም ከአካባቢው አስወጥተዋል።

አዲስ የተነሳው ሰደድ እሳት ሲስፋፋ ነዋሪዎች ቤታቸውን ጥለው ሲሄዱ ወይም በውሃ እሳቱን ለማጥፋት ሲሞክሩ ታይቷል።ደረቃማ በሆነው በዚህ አካባቢ ከፍተኛ ንፋስ መኖሩ ሰደድ እሳቱን ስለሚያቀጣጥለው የአደገኛነት ደረጃው ከፍተኛ መሆኑ ተገልጿል።

ንፋስ በሰዓት ከ20 እስከ 30 ሜትር እየተጓዘ ይገኛል። 31 ሺህ የግድ ከአካባቢው መውጣት እንዳለባቸው ሲነገራቸው ለ23 ሺህ ሰዎች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል።የሎስ አንጀለስ ፖሊስ ኃላፊ ሮበርት ሉና እንዳሉት፣ 500 ታራሚዎች ከአካባቢው እንዲወጡ መደረጉ ተነግሯል።

የሎስ አንጀለስ የእሳት አደጋ ኃላፊ አንቶኒ ማሮን እንዳሉት፣ እሳቱን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ነው።"ወንዙን መሻገር ከቻለ የበለጠ ከባድ ይሆናል" ብለዋል።ከአካባቢው ሸሽታ መንገድ ላይ የምትገኝ ነዋሪ "ከሩቅ ሲታይ በደመና የተዋጠ ነው የሚመስለው። በቅርበት ሲታይ ደግሞ ቀዩ ነበልባል ገሀነም ይመስላል። በጣም አስፈሪ ነው" ብላለች።

ፓሊሳድስ እና ኢቶን ሰደድ እሳቶችን ስታይ ስጋት ገብቷት እንደነበር ተናግራለች። ሰደድ እሳቱ 28 ሰዎችን ሲገድል 10 ሺህ ቤትና ንግድ ተቃጥሏል።"እሳቱ ለምን ደጋግሞ እንደሚነሳ አላውቅም። አስጨናቂ ነው" ብላለች ነዋሪዋ።

የኤንጀልስ ብሔራዊ ፓርክ ቃል አቀባይ ዳና ዲርክስ እንዳለችው፣ በነፋስና በደረቅ ደን ምክንያት እሳቱን ለማጥፋት ቀላል አይሆንም። "በካሊፎርንያ እሳት ዓመቱን ሙሉ ይነሳል" ብላለች።በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ዝናብ እንደሚዘንብ እየተጠበቀ ነው።ከዚህ ቀደም በሰደድ እሳቱ የተቃጠሉ አካባቢዎች በቀላሉ በድጋሚ በእሳት ለመቀጣጠል ተጋላጭ መሆናቸው ተጠቅሷል።ሀገረ ገዢው ጋቪን ኒውሰም ከእሳቱ በኋላ ለሚኖረው ጎርፍና የመሬት መንሸራተት ዝግጅት እንዲደረግ ገንዘብ መድበዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ሦስት የአፍሪካ ሀገራት ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ጥምር ጦር ሊያሰማሩ ነው

በወታደራዊ መንግሥት የሚመሩት ሦስት የምዕራብ አፍሪካ ሀገራት ሽብርተኝነትን ለመዋጋት እና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ የጋራ ጦር ለማሰማራት መስማማታቸው ተገለጸ። ከኒጀር ፣ ቡርኪናፋሶ እና ማሊ የተውጣጡ አምስት ሺህ ወታደሮችን ያቀፈ የጦር ኃይል በቅርቡ የጸጥታ ችግር በበዛበት ማዕከላዊ ሳህል ቀጣና እንደሚሰፍር የኒጀር የመከላከያ ሚኒስትር አስታውቋል።

በአኅራባች ምዕራብ አፍሪካ ሀገራት በፈረንጆቹ 2020 እና 2023 መካከል በተደረጉ ተከታታይ መፈንቅለ መንግሥቶች ወታደራዊ መሪዎች የመንግሥት ሥልጣንን ተቆጣጥረዋል። መንግሥታቱ ባለፈው ዓመት ከአካባቢው አጋሮች፣ፈረንሳይ እና ሌሎች ምዕራባውያን ሀገራት ጋር የቆየውን ወታደራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ካቋረጡ በኋላ የጸጥታ ስጋቶችን በጋራ ለመፍታት ተስማምተዋል።

የኒጀር መከላከያ ሚኒስትር ሳሊፉ ሞዲ አዲሱ ጦር "የሳህል ሀገራት ጥምረት" (ኤኢኤስ) በሚል ስያሜ በሦስቱ ሀገራት ግዛት ውስጥ እንደሚንቀሳቀስ ገልጸዋል። በተጨማሪም ጦሩ የራሱ የአየር ኃይል መሰረተ ልማቶች ያሉት ፣ የጦር መሳሪያ የተደራጀ የስለላ እና መረጃ መረብ የተሟላለት መሆኑን ነው የተናገሩት።

አዲሱ ጥምረት ከሳምንታት በኋላ በተመረጡ ቦታዎች ላይ መሰማራት የሚጀምር ሲሆን፤ ቀደም ብሎ በሦስቱ ሀገራት የጋራ ዘመቻዎች እየተካሄዱ ነው ተብሏል። በምዕራብ አፍሪካ ሀገራት ከአልቃይዳ እና አይኤስ ጋር ግንኙነት ያላቸው ቡድኖች ጋር ለአስርተ ዓመታት በዘለቀው ውጊያ የተቀሰቀሰው ሁከት ከመፈንቅለ መንግሥቱ በኋላም ተባብሶ ቀጥሏል። በቀጣናው እስከ ታኅሣሥ ወር መጨረሻ ድረስ 2 ነጥብ 6 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች መፈናቀላቸውን የተመድ የሰብአዊ ኤጀንሲ (ኦቻ) አስታውቋል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።



# ያለምጥ የተወለደ ልጅ

**ቤዛ እሸቱ**

በሀገራችን አንድም ከፊደል ገበታ "ሀ" ብለው አልያም ከሕይወት "ዋ" ብለው ይማራሉ የሚል አባባል አለ። ይህን እዚህ ጋር ማምጣቴ ምነው መወለድ የግድ በደም ትስስር ብቻ አለመሆኑን የሚገልጽ ተመሳሳይ አባባል በኖረ ለማለት ነው። ዳሩ ከበጎው ይልቅ ፍቅር በግድ መዋለድን ይሻል ማለት ላይ በርትተናል። "ያልወለድኩት ልጅ ቢለኝ አባባ አፌን አለው ዳባ ዳባ" በማለት በፍቅር መዛመድን የሚያጣጥሉ አነጋገሮችን አምጠን ወልደናል። በሀገራችን የሕፃናት ማሳደጊያዎችን የጎበኘ ሰው በተጣሉበት በአውሬ ጉዳት የደረሰባቸው ሕፃናት፣ ከመንገድ የተነሱ እንዲሁም ከሽንት ቤት የወጡ ሕፃናትን ተመልክቶ ማዘኑ የተለመደ ነው።

በቅርብ ጊዜያት ትዝታችን ከተለያዩ ቦታዎች ተጥለው የተገኙ ልጆችና ቤተሰብ ማሳደግ ባለመቻሉ ለተለያዩ ድርጅቶች የተሰጡ ሕፃናት በአብዛኛው በጉዲፈቻ ወደተለያዩ ሀገራት ይሄዱ ነበር። ያኔ ከኢትዮጵያዊነት ተራርቀው ከመልካቸው በራቀ ማህበረሰብ ውስጥ እራሳቸውን በማግኘታቸው ለማንነት ቀውስ ተዳርገው ሀገር ወገን እያላቸው ከወገናቸው ተነጥለው ማደጋቸው የትላንት ትዝታችን ነው። በተቃራኒው ደግሞ ልጅ ፈልገው ግን መውለድ ያልቻሉ በርካታ ጥንዶች ከሀገር ውስጥ እስከ ውጭ ሀገር ሕክምና የአብራካቸውን ክፋይ ፍለጋ ይደክማሉ። ከፍተኛ ገንዘብም ይከሰክሳሉ።

ለጉዲፈቻ ድንበር የተሻገሩ ሕፃናት የራሳቸው ባልሆነ ባሕል እንዲያድጉ እየተደረጉ ለማንነት ቀውስ መዳረግና መሰል ችግሮች መጋለጥን ተከትሎ ከሀገር ውጭ ጉዲፈቻ ሙሉ በሙሉ እንዲቆም ተደርጎ የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻን የሚያበረታታ ሕግ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። የወገናቸውን ልጆች በአካባቢያቸው እንዲያድጉ በማድረግ የኦሮሞ ብሔር አባላት ተጠቃሽ ናቸው። ጉዲፈቻ የሚለው ቃል ከኦሮምኛ ቋንቋ በቀጥታ ወደ አማርኛ የተወሰደ መሆኑንና ትርጓሜውም ተፈጥሯዊ የወላጅነትና የልጅነት የሥጋ ዝምድና ሳይኖር ከሌላ ሰው አብራክ የተወለደን ልጅ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ጥቅሙን ጠብቆ እንደ አብራክ ክፋይ ልጅ ማሳደግ ማለት መሆኑን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፍትሕ ሚኒስቴር መረጃ ይጠቁማል።

በኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የባሕልና ፎክሎር መምህርና ተመራማሪ አቶ ሌኒን ቁጦ ጉዲፈቻ የሚለው ቃል ጉዲሱ ከሚል ቃል መምጣቱን ይናገራሉ። ተመራማሪው ጉዲሱ ማለት ማሳደግ ማለት መሆኑን በመጥቀስ ኦሮሞ የሰው ልጅም ሆነ ሌላ የሚያድግ ነገር ያሳድጋል ይላሉ። ጉዲፈቻ የኦሮሞ ሕዝብ ለሰው ልጅ ፈጥሮ የሰጠው ተቋም መሆኑን የእሳቸውን ጥናት ጨምሮ በርካታ ጥናቶች ማሳየታቸውን ይናገራሉ። የኦሮሞ ማህበረሰብ ጉዲፈቻን ከብዙ ሺ ዓመታት በፊት ጀምሮ ሲጠቀምበት የነበረ አንዱ ተቋም መሆኑን ይናገራሉ።

በማህበረሰቡ ጉዲፈቻ በዋናነት ልጆች ቤተሰብ አጥተው ቤተሰብም ልጆች አጥቶ እንዳይቸገሩ ለማድረግ ጥቅም ላይ መዋሉን የሚናገሩት ተመራማሪው፤ ይህም ልጆች ቤተሰብ አጥተው ያለ አሳዳጊ እንዳያድጉና አሁን ከተማ አካባቢ የሚስተዋለውን ልጆች ወላጅ እያላቸውም ጭምር ተወልደው የሚጣሉበት ሁኔታና ይሄ የሚፈጥረውን ማህበራዊ ቀውስ ለመከላከል አስቀድሞ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሌኒን ማብራሪያ፤ በኦሮሞ ባሕል ልጆች በጉዲፈቻ እንዲሰጡ የሚያደርጉ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው በተለያዩ ምክንያቶች የራሳቸውን ልጅ መውለድ ያልቻሉ ቤተሰቦች ከወንድም፣ ከእህት፣ ከአክስት ወይም ከሌላ ብሔር ልጅን በጉዲፈቻ በመውሰድ አሳድጎ ዘር እንዲቀጥል ለማድረግ ነው። ሌላው ጉዲፈቻ ወሳጁ በስተርጅና እድሜያቸው የሚረዳቸው (ጧሪ) ሰው አይኖርም ተብሎ ሲታሰብ በጉዲፈቻ ልጅ ይወስዳሉ። በተለያዩ ምክንያቶች ልጆች ቤተሰብ በሚያጡበት ወቅት በርካታ ልጅ ያለውም ወላጅ ቢሆን አሳዳጊ ያጣውን ልጅ በጉዲፈቻ ወስዶ ለማሳደግ ይገደዳል።

"በጦርነት ጊዜ ልጆች ቢማረኩ በኦሮሞ ባሕል ባሪያ አይደረጉም" የሚሉት ተመራማሪው ቤተሰቦቻቸው የሚታወቁ ከሆነ ወደቤተሰባቸው እንዲመለሱ ይደረጋል። ከቤተሰባቸው ጋር መቀላቀል ካልተቻለ በጉዲፈቻ የኦሮሞ ማህበረሰብ አባል እንዲሆኑ ይደረጋል። በኦሮሞ ማህበረሰብ አንድ ልጅ በጉዲፈቻ ወደ አንድ ቤተሰብ ሲቀላቀል ትልቅ ዝግጅት ይደረጋል። በዝግጅቱ ላይ አባ ገዳዎች የሀገር ሽማግሌዎች ይገኛሉ። ጉዲፈቻ ትልቅ ነገር ነውና ሥርዓቱ በዘፈቀደ ቀን አይዘጋጅም። ለሥነ-ሥርዓቱ ቀን ከመቆረጡ በፊት ፈጣሪ ምን እያለ ነው? ሥርዓቱ በየትኛው ቀን ቢካሄድ ጥሩ ነው? የሚለውን ለማወቅ በማህበረሰቡ ዘንድ ኮከብና ጨረቃን አይተው የቀን ቆጠራ እውቀት እንዳላቸው የሚታመኑትን አያንቱዎች ያማክራሉ።

በድሮ የኦሮሞ ባሕል የሳምንቱ ቀናት ብዙም ቦታ የላቸውም የሚሉት አቶ ሌኒን በባሕሉ ቀን አቆጣጠር አንድ ወር 27 ቀናት አሉት ይላሉ። አያንቱዎች 27ቱን ቀናት ወይም አያናዎች ቆጥረው በመለየት ይሄ ቀን ጥሩ ነው፤ ይሄ ቀን መጥፎ ነው፤ በማለት ለሠርግ ለጉዲፈቻና ለሌሎችም ዝግጅቶች ተስማሚ የሆኑትን ቀን ይለያሉ። አያንቱዎች ቀን አቆጣጠሩን አይተው ይሆናል ባሉት ቀን የጉዲፈቻ ዝግጅቱ ይካሄዳል። ኮርማ ታርዶ ጉዲፈቻ የምትሰጠው ሴት ልጅ ስትሆን የኮርማው ደም የህጻኗ አንገት ተቀብቶና አንገቷን በእጅ ይዘው ምርቃት ይደረጋል። በጉዲፈቻ የሚወሰደው ወንድ ልጅ ሲሆን የኮርማው ደም ግንባሩ ተቀብቶና ግንባሩ ላይ እጅ ተጭኖ ይመረቃል።

እንደ ተመራማሪው ማብራሪያ፤ በባሕሉ የሴትን ልጅ አንገት ደም መቀባት ትልቅ ምርቃት ነው። ይሄ ለጉዲፈቻ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ልጃገረድ ስታገባ ተመሳሳይ እንደሚደረግና ይህም ብዙ ልጅ እንዲኖራት ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። በተመሳሳይ ወንድ ልጅም ግንባሩ ላይ እጅ ተጭኖ ሲመረቅ እንዲጎብዝ፣ እንዲታይ፣ አዋቂ እንዲሆን፣ ብዙ ልጅና ሀብት እንዲያፈራ ያስችለዋል ተብሎ ይታሰባል። በጉዲፈቻ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ጉዲፈቻ ተቀባይ አካልና የህጻኑ ቤተሰብ በሚታወቅበት ልጁን ለጉዲፈቻ ለማስረከብ ሲስማማ ሰጪም ሆነ ተቀባይ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ በአካል ተገኝተው ቃል ይገባባሉ። በተለይ ጉዲፈቻ ወሳጅ "ከዛሬ ጀምሮ የኔ ልጅ ነው፤ እንደ ልጄ ነው፣ ከልጄ በላይ ነው የማየው ይሄን ልጅ ላይ ልዩነት ካረኩኝ ፈጣሪ ያየኛል። ፈጣሪ ያጥፋኝ " በማለት ቃለ መሃላ ይገባል።

በሥርዓቱ ላይ ጉዲፈቻ የተሰጠው ልጅ የጉዲፈቻ እናቱን ጡት ይጠባል። ይሄም ምሳሌያዊ መሆኑንና ጉዲፈቻ ወሳጆቹ ህጻኑን በጉዲፈቻ የወሰዱት የራሳቸው ልጅ እምቢ ብሎአቸው ከነበረና ከዛ በኋላም ሌላ ልጅ ቢያገኙ እንኳን የወሰዱት ልጅ የበኩር (የመጀመሪያ) ልጅ ሆኖ የሚቀጥል መሆኑን ይናገራሉ። ይህ ሳይሆን ከቀረና የራሳቸውን ልጅ ሲያገኙ በጉዲፈቻ ልጃቸው ላይ ቢቀየሩ ፈጣሪ ይቀየማል እና ልጆቻቸውን ያጠፋል ተብሎ በማህበረሰቡ ዘንድ እንደሚፈራ የሚናገሩት አቶ ሌኒን፤ በተለይ ህጻኑ በትንሽነቱ ለጉዲፈቻ ከተሰጠ ጉዲፈቻ መሆኑን ማወቅ የለበትም ካወቀ ሆዱ ይባባል ተብሎ የጉዲፈቻ ልጅ መሆኑንም ሳይነገረው በፍቅር እንደሚያድግ ይናገራሉ።

በኦሮሞ ባሕል አንድ ሰው ሥነ-ሥርዓቱን አሟልቶ በጉዲፈቻ ወደ ቤተሰቡ ከተቀላቀለ ከወለዱት ልጅ በላይ ነው የሚሉት ተመራማሪው፤ ከቤተሰቡ የተወለደ ልጅ የሚያገኘውን ጥቅም በሙሉ እንደሚያገኝ ያስረዳሉ። በባሕሉ ልጅ ሳይኖራቸው በጉዲፈቻ የሚያሳድጉት ልጅ ከወሰዱ በኋላ የራሳቸውን ልጅ ያገኙ ቤተሰቦች በጉዲፈቻ ያሳደጉት ልጅ የቤቱ የመጀመሪያ ልጅ ሆኖ ይቀጥላል። በዚህም የቤቱ የመጀመሪያ ልጅ የሚያገኘው ጥቅም በሙሉ ይከበርለታል። በባሕሉ በጉዲፈቻ ስለተገኘ በሚል ምንም ዓይነት መድሎ የለበትም።

አንድ ልጅ በጉዲፈቻ አንድ ቤተሰብን ከተቀላቀለ አይገለልም፣ ይሄ በጉዲፈቻ የመጣ ተብሎ ወይም የኛ አይደለም ተብሎ አይነካም የሚሉት አቶ ሌኒን በጉዲፈቻ የተወሰደን ሰው የሰደበ በባሕሉ ትልቅ ወንጀል ስለሆነ ይቀጣል ብለዋል። በኦሮሞ ባሕል በጉዲፈቻ የሚያድግ ልጅን የሰደበ፣ ጥቃት ያደረሰ፣ በድብቅም ቢሆን ለማግለል የሞከረ ሰው "ሲዶምሱ" የሚባል ቅጣት ይጠብቀዋል። "ሲዶምሱ" የኦሮሞ ብሔር ተወላጅነቱ ተወስዶበት እስከ መባረር ድረስ

**በኦሮሞ ማህበረሰብ አንድ ልጅ በጉዲፈቻ ወደ አንድ ቤተሰብ ሲቀላቀል ትልቅ ዝግጅት ይደረጋል። በዝግጅቱ ላይ አባ ገዳዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ይገኛሉ። ጉዲፈቻ ትልቅ ነገር ነውና ሥርዓቱ በዘፈቀደ ቀን አይዘጋጅም**

ሊደርስ ይችላል። በዚህም በጉዲፈቻ የተወሰደን ሰው የነካ ከኦሮሞነት እስከ መባረር የሚደርስ ቅጣት ይጣልበታል። በጉዲፈቻ የተወሰደ ልጅ ምንም ዓይነት መገለልም ሆነ ልዩነት እንደማይደረግና በኦሮሞ ባሕል ትልቁ ሥልጣን እስከሆነው አባገዳ ድረስ ማገልገል እንደሚችል ይናገራሉ። ተመራማሪው ለምርምር ሥራቸው ጥናት በሚያደርጉበት ጊዜ ወደ አምስት የሚደርሱ በጉዲፈቻ ያደጉ ልጆችን ማየታቸውንና ለጥናቱ አላማ የተመለከቷቸው ልጆች ከሌላው ቤተሰብ እኩል ከልጅነት እስከ እውቀት መያዛቸውን መስክረዋል።

ይህ ቀደምት ባሕል አሁን ድረስ መተግበሩን ቀጥሏል። በፊት በባሕል ብቻ ይደረግ የነበረው ጉዲፈቻ አሁን በዘመናዊ መልኩ በሕግና ሥርዓት ተደግፎ ቀጥሏል። የሕፃናት ደህንነትን ከማስጠበቅ አንጻር የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻን የሚከታተለው የኢፌዴሪ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በጉዲፈቻ አፈጻጸም የተሻለ ካላቸው ክልሎች ቀዳሚው ነው። የኦሮሚያ ሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ የሕፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ደክሲሳ በክልሉ በአሁኑ ወቅት የክልሉን የቤተሰብ ሕግና መመሪያውን በመከተል ሕፃናት ከጉዲፈቻ ወላጆች ጋር እንዲገናኙ እየተደረገ መሆኑን ይናገራሉ።

በክልሉ ተጥለው የተገኙ፣ ወላጅና አሳዳጊ የቅርብ ዘመድ የሌላቸው እና ወላጆቻቸው በአቅም ማነስ ማሳደግ ባለመቻላቸው ሌላ ሰው እንዲያሳድጋቸው ፈቃድ የሰጡ ሕፃናት ለጉዲፈቻ እንደሚሰጡ ይጠቅሳሉ። እድሜያቸው አስር ዓመት ከሞላ የጉዲፈቻ ተሰጪ ሕፃናቱም ሃሳብ ይጠየቃል። በጉዲፈቻ ለመስጠት ካልተስማሙ ሌላ አማራጭ ይፈለግላቸዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ በክልሉ ሕፃናትን በጉዲፈቻ ለማሳደግ የፈለገ ጥያቄ አቅራቢ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ሊሆን ይገባል። እድሜው ከ25 እስከ 60 ዓመትና በቂ የገቢ ምንጭ ያለው፤ ከተላላፊ በሽታ እና ከወንጀል ነጻ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

ጉዲፈቻ ጠያቂዎቹ ባልና ሚስት ከሆኑ ሁለቱም ልጅ በጉዲፈቻ ለማሳደግ መስማማታቸውን በጽሑፍ ማሳወቅ አለባቸው ያሉት አቶ ብርሃኑ ጠያቂዎቹ በጉዲፈቻ ልጅ መውሰድ የፈለጉበት ምክንያት ገልጸው በጽሑፍ ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው። ጉዲፈቻ ጠያቂዎቹ ከዚህ በፊት ልጅ(ልጆች) ካላቸው ልጆቻቸው በጉዲፈቻው መስማማት ይኖርባቸዋል። ለዚህም የጽሑፍ ስምምነት ይቀርባል። ጥያቄ አቅራቢው ቤተሰብ ተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በዘርፉ የተመደበ ባለሙያ (ሶሻል ወርከር) የመኖሪያ ቤታቸው ላይ ምልከታ በማድረግ በጉዲፈቻ ለማሳደግ በቂ መሆንና አለመሆናቸውን እንደሚወሰን ይናገራሉ።

እንደ አቶ ብርሃኑ ማብራሪያ፤ ልጆች በጉዲፈቻ መውሰድ ለሚፈልጉ ቤተሰቦች ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ልጅ ከመውሰዳቸው አስቀድሞ በጉዲፈቻ ወስደው ማሳደግ እንዲችሉ የሚያግዝ ሥልጠና ይሰጣቸዋል። አስፈላጊውን መስፈርት ካሟሉና ዝግጅታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ልጅ ለመውሰድ ተራቸው ሲደርስ የጉዲፈቻ ልጁን የሕግ አካላት ባሉበት ቃለ-መሃላ ፈጽመው ይወስዳሉ። በክልሉ ሕፃናት ለጉዲፈቻ ከተሰጡ በኋላም ስለአያያዛቸው ክትትል ይደረጋል። በዚህም ሕፃናቱ በተገቢው መልክ ካልተያዙ ጉዲፈቻው እንዲቋረጥ የሚደረግ ይሆናል። ይህም ቢባል በ2010 ዓ.ም ወለጋ ላይ ለጉዲፈቻ የተሰጠ ሕፃን በተገቢው መልኩ ባለመያዙ መቋረጡን ከመስማታቸው ውጭ ሁሉም ወላጆች የወሰዷቸውን ልጆች በተገቢው መልክ መያዛቸውን ይናገራሉ።

በክልሉ በጉዲፈቻ ለመስጠት ከተዘጋጁ ሕፃናት ቁጥር በላይ ሕፃናቱን በጉዲፈቻ ወስደው ለማሳደግ የተመዘገቡ ሰዎች ቁጥር ይበልጣል። በ2017 ዓ.ም እስካሁን 189 ልጆች በቢሮው በኩል የጉዲፈቻ ወላጅ ማግኘት ችለዋል። በክልሉ 13 ሺ 201 ወላጆች ሕፃናትን በጉዲፈቻ ወስደው ለማሳደግ ቢመዘገቡም የሕፃናቱ ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ተራ በመጠበቅ ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ የጉዲፈቻ ልጅ መብት እንደተወላጅ ልጅ ሙሉ መብቱን ያከበረ ነው።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ሀገር በቀል የትምህርት ሥርዓት...

ከገጽ 5 የዞረ

ይሆንልናል። በተመሳሳይ መልኩ አሁን ያሉን ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን ተቀብለው ለዓመታት በግቢዎቻቸው ያቆያሉ (አሁን ላይ ትንሹ የዩኒቨርሲቲ ቆይታ አራት ዓመት እንደሆነ ልብ ይሏል)። ከዚህ አኳያ፣ የተማሪዎቹን ምደባ ስናከናውን መክረን ዘክረን ተማሪዎቹን በትውልድ መንደራቸው ከሚገኙት ዩኒቨርሲቲዎች ይልቅ ካደጉበት አካባቢ ርቀው በሚገኙ ሌሎች አካባቢዎች በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ውስጥ እንዲመደቡ ብናደርግ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተማሪዎቹ በእነዚህ የዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ወቅት የአካዳሚያዊ አድማሳቸውን ከማስፋት ባለፈ ከሚሄዱበት አካባቢ ነዋሪ ወይም ከተቀባዩ የማህበረሰብ ክፍል ጋር ጠንካራ የእርስ በእርስ ትስስርን ይፈጥራሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎቹ በየመኝታ ቤታቸውም ሲደለደሉ ከተለያየ አካባቢ የመጡ ተማሪዎች ተሰባጥረው እንዲደለደሉ ቢደረግ፤ እነዚህ ከተለያየ አካባቢ የመጡ ተማሪዎች አብረው ስለሚኖሩና በየቀኑ ስለሚገናኙ ይላመዳሉ፣ ሰላምታ ይለዋወጣሉ፤ ክፍል እና ካፌ አብረው ይሄዳሉ፣ በውጤቱም አብሮነታቸው ይጠነክራል።

ይሁን እንጂ፣ የተመኘነውን የሕዝብ አንድነት ለማምጣት የሚያስችል ውጤታማ ዘዴን ለመንደፍ እና እስከ ግቡ ለማድረስ ከፍተኛ ብልሃትን ይጠይቀናል። ይህን የሕዝብ አንድነት የማነጽ ዓላማ በሚገባ ለመተግበር ተማሪውን ከቀዬው አርቆ መመደቡ ብቻ በቂ አይሆንም፣ ይልቁንም፣ የተቀባዩን የማህበረሰብ ክፍል መልካም ፈቃድ፣ ትብብር እና እገዛም ይፈልጋል። በዚህ ረገድ፣ ብዙውን ጊዜ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በአካባቢያቸው ዩኒቨርሲቲዎች እንዲቋቋሙላቸው ሲጠይቁ እንሰማለን። ይህ ከሆነ ዘንድ ደግሞ በምትኩ እነዚህ የአካባቢው ነዋሪዎች በመካከላቸው ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ ከሩቅ አካባቢዎች የሚመጡ እንግዳ ተማሪዎችን በቅጡ ማስተናገድ እና መደገፍ አለባቸው። ይህን ከነሱ መጠበቅ ምክንያታዊ ነው። የሞራል ግዴታቸውም እንደሆነ ዕውቂያ ሊሰጥ ይገባል። ስለዚህ፣ ማህበረሰቡ ከሱ የሚጠበቀውን ሳያደርግ ዩኒቨርሲቲ ይቋቋምልኝ ብሎ የመጠየቅ ሞራላዊ ቁመና ሊኖረው ከቶ አይችልም ማለት እንችላለን።

በምትኩ ግን፣ እንግዶቻቸውን (በተለይ ከሩቅ አካባቢ የሚመጡ ተማሪዎቻቸውን) በቅጡ የማያስተናግዱ አካባቢዎች ካሉም ተቋማቱን በመዝጋት እና በጀታቸውንም፣ ተማሪዎቻቸውንም እንግዳ ተማሪዎቻቸውን በቅጡ ለሚያስተናግዱ ተቋማት በመስጠት ተጠያቂነትን ማስፈን ይቻላል። ተቋማቱ በአካባቢው እንዲሆኑለት የፈለገ ማህበረሰብ ልጆቹን በቅጡ ይያዝ የማለትን ያህል ሃሳብ ይገልጣል።

ይህ ተማሪዎቹን የማስተናገድ ልማድ ባቅም የሚከወን፣ በየአጋጣሚው የሚፈጸም እንጂ የዕለት ተዕለት መሆን የግድ የለበትም። በበዓላት ቀን ልጆቹን ጠርቶ አብሮ የማክበር ወይም አልፎ አልፎ (በየተወሰነ ጊዜ) ወይም በየአጋጣሚው ልጆቹን ጠርቶ አብሮ የማሳለፍ አይነት የቀለለ ተግባር መሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ልማድ ተማሪዎቹ ላይ የቤተኛነት ስሜት እንዲፈጠርባቸው ማስቻል ብቻ ሳይሆን በእነዚህ በሚቆዩባቸው ዓመታት ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በጥልቅ እንዲቆራኙ ያስችላቸዋል።

በዚህ ረገድ፣ ሕዝቡ እንኳ በግልም ሆነ በማህበር የሚያደርጋቸው አንዳንድ ጥረቶች አሉ፣ በመንግሥታዊ ፖሊሲዎች ሲታገዙ አይስተዋልም እንጂ። ለዚህም እንደ ማሳያ ለማቅረብ የምፈልገው፣ የሚከተለውን ከማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያገኘሁትን ምስክርነት ነው - “ልጁ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሁሉም ተማሪ ለበዓል ወደ ቤተሰብ ሄደው ብቻውን ቀርቷል ... ደበረኝ አለ ... ብዙ ግብረመልስ ተሰጥቷል ... አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከሆንክ መጥቼ ልውሰድህ፣ እኛጋ አሳልፍ ... ሐሮማያ ከሆንክ በዚህ ስልክ ደውልልኝ፣ አብረን ዘና እንላለን... ወልቅጤ ከሆንክ በናትህ ና ቤታችን ምናምን ጋር ነው ...አርባ ምንጭ ከሆንክ.... መጥቼ ልውሰድህ አብረን እንቋደስ ጎንደር .... ወሎ ፣ ጋምቤላ ...ያልተጠቀሰ ሀገር ያልተጠራ ዩኒቨርሲቲ የለም። ሁሉም ይሄን ከየት እንደመጣ ማን እንደሆነ የማያውቁትን ተማሪ በዓልን ከእነሱ ጋር እንዲያሳልፍ ከልባቸው እየጋበዙት ነበር”።

ይሁን እንጂ፣ ይህ ሕዝቡ በግሉም ሆነ በማህበር የሚያደርጋቸው ጥረቶች ከፍሬ የሚደርሱት በመንግሥታዊ ፖሊሲዎች፣ ሥርዓቶች፣ መዋቅሮች እና ጥረቶች ሲታገዙ ነው።

ወደ ስር ነገሬ ስመለስ፣ የእነዚህ ባህላዊ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የእለት እንጀራቸውን ፍለጋ አኮፋዳቸውን ይዘው መንደር ለመንደር በመዞር ይለምናሉ። በዚህም ሳቢያ፣ ምናልባት እንደ ማህበር፣ ተስካር፣ ክርስትና ባሉ አልያም በሌሎች ሃይማኖታዊ በዓላት ወይንም ሕዝባዊ መሰብሰቢያዎች ወቅት ወደ መንደሩ ነዋሪ ቤት ጎራ እንዲሉ ሊጋበዙ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም፣ በእንደዚህ አይነቱ መስተጋብር የሚፈጠር ትስስር እምብዛም ጠንካራ ሲሆን አይስተዋልም። በምትኩ ግን፣ ዛሬ ላይ መክረን ዘክረን፣ አቅደን፣ ተነጋግረን፣ ተወያይተን፣ በከፍተኛ ብልሃት እና በብዙ ማስተዋል የተሻለ፣ ጠንካራ፣ የረጋ እና ዘላቂ የተማሪ-ማህበረሰብ ትስስር ማጎልበቻ ዘዴ ወይም ሥርዓት (የሩቅ ጊዜ ግቡም የሕዝብን አንድነት ማጽናት የሆነ) መንደፍ እንችላለን።

ይህን ዘዴ በተመለከተ፣ ለምሳሌ በአካባቢው ነዋሪዎች መካከል ረዘም ላለ ጊዜ ለትምህርት የሚቆዩ ለአካባቢው እንግዳ የሆኑ የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎች በሃይማኖታዊ በዓላት ወይንም ሕዝባዊ መሰብሰቢያዎች ወቅት በመንደሩ ነዋሪዎች የሚጋበዙ/የሚጠሩ መሆን አለባቸው። ለምሳሌ፣ ተማሪዎቹ ክርስቲያን ከሆኑ እንደ ማህበር፣ ተስካር፣ ክርስትና ባሉ አልያም ሌሎች ሃይማኖታዊ በዓላት ላይ የሚጋበዙ/የሚጠሩ መሆን አለባቸው፤ ሙስሊም የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ረመዳን እና ሰደቃ በመሳሰሉት ሃይማኖታዊ በዓላት ላይ እንዲሳተፉ የሚጋበዙ መሆን አለባቸው። ስለዚህ፣ እነዚህ ተማሪዎች በአቅራቢያ ባሉ የመንደር ነዋሪዎች የሚጠሩ፣ ማዕድ አብረው የሚቋደሱ፣ በማህበራዊ መስተጋብር የሚሳተፉ፣ በተጨማሪም፣ በአቅራቢያ ያሉ መንደሮች ያለስጋት ጎራ ብለው ወደ ካምፓስ መመለስ የሚችሉ መሆን አለባቸው። ከዚህም በላይ፣ ይህ ዘዴ ከሃይማኖት እና ከቋንቋ ድንበር በላይ ተደርጎ ተሻሽሎ እና ዘምኖ ጥልቅ ማህበራዊ መስተጋብርን እና ትስስርን እንዲያጠናክር ታልሞ ሊዋቀርና ሊነደፍ ይችላል።

በመሠረቱ፣ ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከ42 በላይ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች አሏት። ስለዚህ እንዲህ ቢሆን ብላችሁ አስቡ። የወለጋ ተማሪ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሲመደብ እና ከጎንደር ማህበረሰብ እና ባህል ጋር ለዓመታት ሲቆይ፣ ተማሪው ከጎንደር ጋር ጥልቅ ትስስርና ረቂቅ የማንነት ግንኙነት ያዳብራል። በተመሳሳይ መልኩ፣ በሌላ የሀገሪቱ ክፍል የሚመደብ የጎንደር ተማሪ ከሚመደብበት አካባቢ ማህበረሰብ እና ባህል ጋር ተመሳሳይ ትስስርን ይፈጥራል። ስለዚህ፣ በዚህ መንገድ የክልል ድንበሮችን የሚሻገር የሕዝብ ትስስርን እና አንድነትን ማጎልበት እና ማጠናከር እንችላለን።

ነገር ግን፣ ነገሩ እንዲሁ ላይ ላዩን የይምሰል፣ የታይታ፣ የግብር ይውጣ፣ መናኛ፣ ውሸልሸል እንዳይሆንብን ያሰጋል። በመሆኑም፣ ይህን ዘዴ በሚገባ ለመንደፍ፣ ነድፎም ለመተግበር እና በውጤቱም የምንመኘውን አንድነት ለማምጣት በብዙ ጥንቃቄ፣ በብዙ ማስተዋል፣ እና በከፍተኛ ብልሃት መከወን አለበት። ልክ ለትምህርቱ ብዙ ሀብት እንደምንመድበው ለዚህም ዓላማ መሳካት ከፍተኛ ሀብት ተመድቦለት የሚከናወን መሆን አለበት። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ብልሃቱ/ዘዴው የጠነከረ አብሮነትን፣ ጥልቅ ማህበራዊ መስተጋብርን፣ ብሎም የተፈለገውን የሕዝብ አንድነት ማቀጣጠል ይቻለዋል።

እንዴት ይኼ የተመኘነው የሕዝብ አንድነት፣ ትስስር፣ እና ዝምድና ላይ ላዩን ሳይሆን ስር ሰዶ፣ የይምሰል ሳይሆን የምር፣ ተውሸልሽሎ ሳይሆን በጠንካራ እና በረጋ መሰረት ላይ፣ ብሎም ትርጉም ባለው መንገድ ሊበቅል ይችላል? ብሎ መጠየቅ እዚህ ላይ የሚገባ ነገር ነው። በዚህ ረገድ፣ ማለትም እንዴት ይህ እንደሚከናወን ፍንጭ የሚሰጡን፣ ልምድ የምንቀስምባቸው፣ ተሞክሯቸውን የሚያጋሩን፣ ብልሀት የሚያቃብሉን የተለያዩ ሀገር በቀል ልማዶች፣

**የሕዝብ አንድነት ለማምጣት የሚያስችል ውጤታማ ዘዴን ለመንደፍ እና እስከግቡ ለማድረስ ከፍተኛ ብልሀትን ይጠይቀናል። ይህን የሕዝብን አንድነት የማነጽ ዓላማ በሚገባ ለመተግበር ተማሪውን ከቀዬው አርቆ መመደቡ ብቻ በቂ አይሆንም፣ ይልቁንም፣ የተቀባዩን የማህበረሰብ ክፍል መልካም ፈቃድ፣ ትብብር እና እገዛም ይፈልጋል**

ሲስተሞች(የሃሳብ ሕንፃዎች)፣ ተሞክሮዎች እና ጥረቶች አሉ።

ከእነዚህ ነባር ልማዶች መካከል ሃሳቤን በተጨባጭ የሚያስረዳልኝን አንድ ማሳያ አቀርባለሁ። ይኸውም፣ ከራስ ያልተወለደን ሰው ጡት (አውራ ጣት) አጥብቶ ልጅ የማድረግ፣ ረዳት ዘመድ ወገን የማግኛ ነባር ልማድ - የ"ጡት አባት" የተሰኘው ነባር ልማድ ነው። ጉዲፈቻም በተመሳሳይ። በዚህ "ጡት አባት" ልማድ የሚገለጠውን ሃሳብ ከማየታችን በፊት ልማዱ ለአንዳንድ አንባቢያን የማይታወቅ ሊሆን ስለሚችል እነርሱን ለመርዳት ያህል ስለ ኃይለ-ቃሉ ትርጓሜ ላስቀድም።

ጡት አባት - እንደአብነት:-

የ"ጡት አባት" ልማድ በክፉ ጊዜ መጠጊያና መማፀኛ እንዲሆነው፣ በክፉ ጊዜ የችግር ረዳት እንዲሆነው፣ የጡት ልጅ የጡት አባትን ጡት ጠብቶ ወገንና ዘመድ ጥግ የማድረግ ልማድ ነው። ልማዱ ረዳት ዘመድ ወገን የማግኛ ነባር ልማድ ነው። በሂደቱም የጡት አባት የዝምድና አባት ይሆናል። (ከሳቴ ብርሃን ተሰማ ፣652፣ 690) በተጨማሪም፣ ልማዱ ልጅን የአደራ ልጅ አድርጎ ለጡት አባት የመስጠት፤ በዚህም ሳቢያ፣ የራስ ያልሆነን ልጅ የአደራ ልጅ የማድረግንም ልማድ ይጨምራል። (ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን፣221-22)

ልማዱ በሀገራችን ረጅም ዘመናትን የዘለቀ ሲሆን፤ ሥርዓቱ የሚከናወንበትም የራሱ የሆነ ሥነ ሥርዓት አለው። በእዚህ የመዛመድ ሥነ-ሥርዓት ላይ የጡት ልጅ የጡት አባትን በማር የተነከረ አውራ ጣት ይጠባል፣ በውጤቱም፣ ጡት ተጣቡ አባትና ልጅ ተኳኳኑ የማለትን ያህል ሃሳብ ይገልጣል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች የጡት-አባት ጡቱን አጥብቶ ልጅ የማድረግ ነገር ቢስተዋልም፣ ነገሩ ተምሳሌታዊ ነው። የጡት መጣባት ሃሳባዊ ተምሳሌቱ መዛመድን፣ መቀራረብን፣ ከተፈጥሯዊ ወላጅነት ጋር የሚቀራረብ ትስስር መፈጠርን ለማሳየት ይውላል። የዚህ ልማድ ዋናው ዓላማ በጡት ልጅ እና በጡት-አባት መሃል ያለውን ስሜታዊ ትስስር በማጠናከር በመካከላቸው ጠንካራ እና ዘላቂ የአባትና ልጅ ግንኙነት መፍጠር ነው። ከዚህ አኳያ፣ ይህ የመዛመድ ልማድ ጠንካራና ዘላቂ የቤተሰብነት ትስስርን መፍጠር በመቻሉ በማህበረሰቡ ዘንድ በጣም የሚከበር ለመሆን በቅቷል።

ከልማዱ ለምሳሌ በዚ መልኩ ዘዴ ልንቀምምበት እንችላለን። ለምሳሌ፣ ተማሪዎቹን በአቅራቢያ ካሉ የመንደር ነዋሪዎች ጋር ጡት አጣብተን (ሃሳባዊ ተምሳሌት ነው) ልናስተሳስራቸው እንችላለን። ይህም ማለት፣ ለማህበረሰቡ እንደየአቅሙ አንድም ሁለትም ተማሪዎች በአደራ ልጅነት ብንሰጠው፣ በሁለቱ መካከል በአመዛኙ ጠንካራ የቤተሰብነት ትስስር ይፈጠራል። በውጤቱም፣ ብዙ ትርፋማ የሚሆን መስተጋብር፣ ትስስር፣ እና ዝምድና ለመፍጠር ያስችለናል።

በተጨማሪም፣ ይህ በተማሪዎቹ እና በአካባቢው ማህበረሰብ መካከል የሚፈጠር መስተጋብርም ሁለቱም የሚያተርፉበት ነው የሚሆነው። ይህም ማለት፣ እነዚህ የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎች በአቅራቢያ ባሉ የመንደር ነዋሪዎች የሚጠሩ ከሆነ፣ ማዕድ አብረው እንዲቋደሱ የሚጋበዙ ከሆነ፣ ብቅ ብለው ቡና እንዲጠጡ የሚጠሩ ከሆነ፣ በምላሹ እነሱ ደግሞ እቤት ያሉትን ልጆች ያስጠናሉ። ከሁሉም በላይ ግን፣ በሁለቱ መካከል የሚፈጠር ጥልቅ መስተጋብር ወደ ላቀ ወደሚበልጥ ዘላቂ ጥቅም ያመራል።

ለማጠቃለል፣ እነዚህና መሰል ጠቃሚ ተሞክሮዎች በዘመናዊው ማህበረሰብ ውስጥ በውጤታማነት ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው። በመሆኑም፣ እንደዚህ ያሉ ጠቃሚ ሀገር በቀል እሴቶች በቅጡ ተለይተው፣ በጥንቃቄ ተመርምረው፣ ተስተካክለው፣ ተሻሽለው እና ዘምነው በዘመናዊ አውዶች ላይ መተግበራቸው በእጅጉ የሚበጅ ተግባር ነው የሚል እምነት አለኝ። ስለዚህ፣ እነደዚህ ያሉ ጠቃሚ ተሞክሮዎችን ለዘመናዊ የሕይወት አውዶች እንዲሆኑ አድርገን አሻሽለንና አዘምነን ስንተገብር ለህይወት ዘመን የሚቆይ የሕዝብ ትስስርን፣ መተሳሰብን፣ አብሮነትን፣ እና አንድነትን እናሰፍናለን።

# የዲጂታል ቴክኖሎጂ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ያደረጉት የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መላኩ ፈንታ እንደተናገሩት፤ የወንጀል መከላከልና የምርመራ ሥራዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በላቀ ሙያዊ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች እየተከናወኑ ይገኛል።በተለይ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ በተቋማቱ በተደረገው የሪፎርም ሥራ ወንጀሎችን ቀድሞ መከላከልና ተፈጽመው ሲገኙም በላቀ የምርመራ ብቃት ተጣርቶ ለፍርድ የማቅረብ ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ምክትል ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።እንደ ምክትል ኮሚሽነር መላኩ ገለጻ፤ ተቋሙ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር የተቋቋመ እንደመሆኑ የዘመነ የፖሊስ ተቋም ለመሆን በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል።በዚህም የወንጀል መከላከልና የምርመራ ሥራዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የላቀ ሙያዊ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲከናወኑም ማድረግ ችሏል።

በጉብኝቱ ላይ ተገኝተው ስለ ተቋማዊ አሠራርና የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ብሎም አበርክቶ ማብራሪያ የሰጡት ኢንስፔክተር አንድነት ሲሳይ በበኩላቸው፤ "የዜጎች ተሳትፎ ማረጋገጫ የሞባይል መተግበሪያ" እና የመንገድ ዳር የደህንነት ካሜራዎች ለወንጀል ምርመራ ጥራትና ፍጥነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆኑን አብራርተዋል።

ግንቦት 16/2016 ዓ.ም ዲጂታል የሞባይል መተግበሪያው በይፋ ሥራውን እንደጀመረ የሚናገሩት ኢንስፔክተር አንድነት፤ ተቋሙ በመተግበሪያው አማካኝነት ከማህበረሰቡ የወንጀል ጥቆማዎችን በድምፅ፣ በጽሑፍ መልእክቶች፣ በፎቶዎች፣ በተንቀሳቃሽ ምስሎችን እና ፋይሎችን እንደሚቀበልና ምርመራ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል። በዚህም ከማዕከል የደረሱ ጥቆማዎች ያሉበት ሂደት በግልፅ ስለሚታይ ጥቆማዎቹ ላይ ምርመራ ሳይደረግባቸው ረጅም ጊዜ ከወሰዱ ምርመራውን የሚያከናውኑ ጣቢያዎችን ተጠያቂ የሚያደርግ አሠራር መዘርጋቱንም ገልጸዋል።

እንደ ሞባይል መተግበሪያው ሁሉ፣ የመንገድ ዳር የደህንነት ካሜራዎች የወንጀል ምርመራ ጊዜን ማፋጠናቸውን እና ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ጥራት እንዲጨምር ማድረጋቸውንም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ የኦፕሬሽን ዋና መምሪያ ኃላፊ አቶ ሙሊሳ አብዲሳ በበኩላቸው፤ ተቋሙ የሽብር ወንጀል፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ በፋይናንስ ተቋማት ላይ የሚፈጸመውን ጨምሮ ሌሎች ትላልቅ ወንጀሎችን የማጣራት ተግባራት እንደሚያከናውን አብራርተዋል።በዚህም ከባድ ወንጀሎችን በማጣራትም ውጤታማ ሥራ መሥራቱ እና ከሰብአዊ መብት ጥሰት በፀዳ መልኩ ምርመራዎች እንደሚካሄዱ አስረድተዋል።



በጉብኝቱ የፌዴራል ፖሊስ የሚጠቀምባቸው የከባድና ቀላል ተሽከርካሪዎች፣ የአድማ መበተኛ መሣሪያዎች፣ ኮማንድ ኮንትሮል ሲስተም፣ የመገናኛ ሬድዮ መቆጣጠሪያ ክፍል፣ የፀረ ፈንጂ እና የአደንዛዥ እፅ ቁጥጥር እና ምርመራን ጨምሮ፤ በተቋሙ እየተሠሩ የሚገኙ ዘመናዊ የወንጀል መከላከልና የምርመራ ሥራዎች በጋዜጠኞች ተጎብኝተዋል።


## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | |
|---|---|
| 1. ስም:- ካናን ክርኤቲቭ ኮ. ኤልቲዲ (CANAAN CREATIVE CO., LTD.) አድራሻ:- Room 2001, 20th Floor, Building 1, Yard 1, No. 81 Beiqing Road, Haidian District | |
| 2. ማመልከቻው የገባበት ቀን | 08/12/2023 |
| 3. ማመልከቻ ቁጥር - | FTM/14685/23 |
| 4. የንግድ ምልክቱ መግለጫ:- | የምስል |
| 5. የንግድ ምልክቱ - | |
| 6. አለም አቀፍ ምድብ:- | 09 እና 42 |

**ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች፤**

**ምድብ 09-** የኮምፒተር ሶፍትዌር፣ የተቀዳ ኮምፒውተሮች; የኮምፒዩተር መለዋወጫ መሳሪያዎች፣ የዳታ ማቀነባበሪያ መሳሪያ ማቀነባበሪያዎች [የማዕከላዊ ማቀነባበሪያ ክፍሎች]፤ ካፐለሮች [ዳታ ማቀነባበሪያ መሳሪያዎች] ኢንተግሬትድ ሰርከውት ካርዶች [ስማርት ካርዶች]፤ ለኮምፒውተሮች ኢንተርፌሶች፣ ኢንተግሬትድ ሰርከውቶች፤ ቺፕሶች [ኢንተግሬትድ ሰርኪውቶች]፤

**ምድብ 42-** የኮምፒተር ሶፍትዌር ኪራይ፤ የኮምፒተር ሶፍትዌር ንድፍ፤ የኮምፒተር ፕሮግራሚንግ ፤ መረጃን ወይም ሰነዶችን ከአካላዊ ወደ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መለወጥ፤ የቴክኖሎጂ ምርምር፤ የዳታ ኢንክሪፕሽን አገልግሎቶች ለኮምፒዩተር ደህንነት እና ለአደጋ መከላከል የሶፍትዌር ጥገና፣ የኮምፒዩተር ሶፍትዌርን ማዘመን፤ የኮምፒተር ፕሮግራሞችን እና መረጃዎችን መለወጥ፣ ከአካላዊ ለውጥ ሌላ፤ ለሌሎች ሰዎች አዳዲስ ምርቶች ምርምር እና ልማት ናቸው::

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል።ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰውን የንግድ ምልክት በምዝገባ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን በስተቀር ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናሳውቃለን።**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN Vol LXXXIV No 136-16/5/2017 (24 /1/2025 )



## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም፡- ጉሊት በገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>የአመልካች አድራሻ፡- ሐይቅ ዳር ሀዋሳ ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር፡-LTM/17102/2016<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን ፡- 26/10/2016 E.C | | |
| 3 | ምልክት፡- Gulit Saving & Credit Cooperative Association Small Things Matter! | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡- የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡- (Saving & Credit Cooperative Association) |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | የብድርና ቁጠባ አገልግሎት (ምድብ 36) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል።ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ሕግ ይጠየቃል።**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN Vol LXXXIV No 136-16/5/2017 (24 /1/2025 )



## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም የ.ሀ.ኤኑአ.የተ.የግ.ማ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-09774 የተሽከርካሪው ዓይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር MMI/TRD10245A ሞዴል MMT/TRD የሞተር ቁጥር Trailer ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ24/4/2017 ዓ.ም አመልክተዋል።ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**



የባለንብረት ስም ያ ሀ ኤ ኑ ኃ/የተ/የግ/ማ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-40027 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJME3TRS30C-221648 ሞዴል AT380T38H የሞተር ቁጥር 137383 የሊብሬ ቁጥር E0106465 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ23/4/2017 ዓ.ም አመልክተዋል።ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርኮሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

# ስፖርት





# የአዲስ አበባ ፖሊስ የስፖርት ፌስቲቫል ነገ ይጀመራል

**ብርሃን ፈይሳ**

የአዲስ አበባ ከተማ አቀፍ የፖሊስ ሠራዊት ስፖርታዊ ውድድር እና ፌስቲቫል ነገ እንደሚጀምር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አስታወቀ። የውድድሩ መካሄድ በስፖርት እድገት አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም ይጠበቃል።

ለረዥም ጊዜ ተቋርጦ የቆየው የአዲስ አበባ ከተማ የፖሊስ ሠራዊት ስፖርታዊ ውድድርና ፌስቲቫል በአዲስ መልክ ሲጀመር፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ እንዲሁም የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አዘጋጅነት ከነገ ጥር 17/2017 ዓ.ም አንስቶ ለቀጣይ 15 ቀናት እንደሚቆይ ተጠቁሟል።

ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደው ይህን ውድድር እና ፌስቲቫል አስመልክቶም በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ውይይት ተካሂዷል። በውይይቱም የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌቱ አርጋው፣ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀንን ጨምሮ ከሁለቱ ተቋማት የተወጣጡ አመራሮች ተገኝተዋል።

ስፖርት እና ፖሊስ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ገጽታ እንደመሆናቸው በቀደመው ዘመን በተለይም በደርግ ዘመነ መንግሥት  በሀገር አቀፍ ደረጃ በየእርከኑ በፖሊስ ሠራዊቱ መካከል ደማቅ ስፖርታዊ ውድድሮች ይደረጉ ነበር። በዚህም ኢትዮጵያን እስከ ማስጠራት የደረሱ በርካታ ስፖርተኞችን ማፍራት ተችሏል። ይሁን እንጂ የሠራዊቱ የስፖርት ክለቦች እንጂ በሠራዊቱ መካከል የሚደረጉት መሰል ውድድሮች ላለፉት በርካታ ዓመታት እንደ ሀገር ተቀዛቅዘው፣ በከተማዋ ደግሞ ተቋርጠው ቆይተዋል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር



**ፌስቲቫሉ የፖሊስ ሠራዊት በኢትዮጵያ ስፖርት እድገት አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ታምኖበታል፣**

ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ከፖሊስ ኮሚሽኑ ጋር ባደረገው ውይይት ግን የፖሊስ ሠራዊቱን ውድድርና ፌስቲቫል በአዲስ መልክ ለማስጀመር ተችሏል። ይህም በሀገር ሁለንተናዊ የስፖርት እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ተጠቁሟል። የውድድሩ ዋና ዓላማ በሠራዊቱ መካከል ትስስርን መፍጠር ሲሆን፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ  ለሚዘጋጀው የፖሊስ ሠራዊት ስፖርታዊ ውድድር (ከየካቲት 21-30/2017 ዓ.ም) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን በየስፖርት ዓይነቱ የሚወክሉ ስፖርተኞችን ለመምረጥም ያግዛል፡፡

ለዓመታት ተቋርጦ የነበረው የፖሊስ ሠራዊት ስፖርታዊ ውድድር እና ፌስቲቫል መጀመሩ ለከተማው ብሎም ለሀገር ሁለንተናዊ የስፖርት እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት በመድረኩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌቱ አርጋው ገልጸዋል። ፖሊስና ስፖርት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደመሆናቸው ውድድሮችን መዘጋጀታቸው ስፖርቱን ባሕሉ ያደረገ፣ ብቁ፣ ጠንካራና ፖሊሳዊ አቋም ያለው ሠራዊት ለመፍጠር እንደሚያግዝም አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ በላይ ደጀን በበኩላቸው የሀገራችንን ስም እና ሰንደቅ ዓላማ በዓለም የስፖርት የውድድር መድረክ ከፍ ያደረጉ በርካታ ስፖርተኞች ከፖሊስ ሠራዊት መውጣታቸውን አስታውሰው፤ በቀጣይ የፖሊስ ስፖርታዊ ውድድሮች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

ውድድሮቹ በ8 የስፖርት ዓይነቶች (አትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ ቮሊቦል፣ ኢላማ ተኩስ፣ ዳርት፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ቦክስ እና ገመድ ጉተታ) በሁለቱም ጾታ እንደሚካሄድና ፲፩ዱም ክፍለ ከተሞች እንዲሳተፉበትም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የፖሊስ ሠራዊት በኢትዮጵያ የስፖርት እድገት ላይ የራሱን ዐሻራ ያስቀመጠ እና የሀገርን ስም እና ሰንደቅ ዓላማ በዓለም የውድድር መድረክ ከፍ ብሎ እንዲጠራ ያደረጉ ስፖርተኞችን ያፈራ ተቋም መሆኑ ይታወቃል። ይህንን መሰል ስፖርታዊ ውድድሮች በድጋሚ መዘጋጀታቸውም በፖሊስ ሠራዊቱ መካከል ጓዳዊ ትስስርን እንደሚያጠናክር ይታመናል። በመሆኑም ተቋርጦ የነበረውን ከተማ አቀፍ የፖሊስ ሠራዊት ስፖርታዊ ውድድር ለማስጀመር በክፍለ ከተማ ደረጃ የውስጥ ውድድሮች ሲካሄድ መቆየቱን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የተገኘው መረጃ አመልክቷል።

በፌስቲቫሉ ከስፖርታዊ ውድድር በተጨማሪ የተለያዩ ወታደራዊ የሰልፍ ትርኢቶች፣ በፖሊስ የሰለጠኑ የእንስሳት ትርኢቶች እና የተሽከርካሪ ትርኢቶች የሚቀርቡ መሆኑ በውይይቱ ላይ የተጠቆመ ሲሆን የከተማዋ ነዋሪ በመክፈቻ መርሃ ግብሩ ላይ እንዲታደምም ጥሪ ቀርቧል።


## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | |
|---|---|
| 1. ስም:- ኪንግስ ኤጁኬሽን ሊሚትድ (KING'S EDUCATION LIMITED) አድራሻ:- Sixth Floor, 3 Burlington Gardens, LONDON W1S 3EP, United Kingdom | |
| 2. ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን | 09/04/2024 |
| 3. ማመልከቻ ቁጥር፡- | FTM/14985/24 |
| 4. የንግድ ምልክቱ መግለጫ፡- | የቃል |
| 5. የንግድ ምልክቱ - | **KING'S COLLEGE** |
| 6. የብቸኝነት መብት ያለመጠየቅ | **COLLEGE ለምድብ 41** |
| 7. አለም አቀፍ ምድብ፡- | 09፣16፣25 እና 41 |

**ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች፤**

**ምድብ 09-** ሊወርዱ የሚችሉ ኤሌክትሮኒክ ህትመቶች ኢንተራክቲቭ የኤሌክትሮኒክስ ህትመቶች፣ በኤሌክትሮኒክ ፎርማት ውስጥ የመመሪያ ማኑዋሎችዎች ኢ-መጽሐፍት፤ ሊወርዱ የሚችሉ ኤሌክትሮኒክ መጻሕፍት፣ ከበይነመረቡ ሊወርዱ የሚችሉ ዲጂታል መጽሐፍት፤ የድምጽ መጽሐፍት፤ የንግግር መጽሐፍት; ኤሌክትሮኒክ መጽሔቶች፤ የመመሪያ እና ማስተማሪያ አፓራተሶች እና መሳሪያዎች የማስተማሪያ አፓራተሶች ሊወርዱ የሚችሉ ፖድካስቶች፤ ሊወርዱ የሚችሉ የመልቲሚዲያ ፋይሎች! የስልጠና ሶፍትዌር፤ ኢንተራክቲቭ ሶፍትዌር፣ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ላይ የተመሰረተ ኢንተራክቲቭ ሶፍትዌር፣ ምናባዊ የመማሪያ ክፍል ሶፍትዌር፤ ለትምህርት የሚሆን ምናባዊ ሪያሊቲ _ ሶፍትዌር፣ ሊወርዱ የሚችሉ የኮምፒውተር ሶፍትዌር መተግበሪያዎች፤ ትምህርታዊ የሞባይል መተግበሪያዎች፤

**ምድብ 16-** ወረቀት እና ካርቶን፤ የታተመ ነገር፤ የመፅሃፍ ማሰሪያ ቁሳቁስ፣ ፎቶግራፎች [የታተሙ] የጽህፈት መሳሪያ፣ ለጽህፈትመሳሪያ ወይም ለቤት ውስጥ ዓላማዎች የሚውሉ ማጣበቂያዎች፤ የአርቲስቶች እቃዎች፤ የቀለም ብሩሽዎች፤ ታይፕራይተሮች፣ የኤሌክትሪክ ወይም ኤሌክትሪክ ያልሆኑ እና የቢሮ ፍላጎቶች፣ ከቤት ዕቃዎች በስተቀር፤ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች (ከአፓራተስ በስተቀር)፣ የማተሚያ ዓይነት ማተሚያ ብሎኮች የታተሙ ህትመቶች ፔሬዲካልስ፤ የመማሪያ መጽሐፍት፣

ምድብ 25- አልባሳት፣ ጫማ፣ የራስ መሸፈኛ የትምህርት ቤት ዩኒፎርም፤ ሸሚዞች ፤ ቲ-ሸርቶች፤ ጀርሲዎች [ልብስ የፖሎ ሸሚዞች ፤ ቀሚሶች፤ ሱሪዎች፤ ለጂምናስቲክ የሚሆን ልብስ፣ ጃኬቶች [ልብስ]; እስቶኪንጎች፤ የመታጠቢያ ክዳን፤

**ምድብ 41-** የመዝናኛ እና የትምህርት አገልግሎቶች፣ ትምህርትን በተመለከተ መረጃ፤ ከኮምፒዩተር ዳታቤዝ ወይም ከበይነመረቡ በመስመር ላይ ከተሰጠው ትምህርት ጋር የተያያዘ መረጃ ፊት ለፊት ትምህርታዊ መድረኮችን ማደራጀት እና ማካሄድ፣ የስልጠና አውደ ጥናቶች፣ ኮሎኪዩሞች፣ ኮንፈረንሶች፣ ሴሚናሮች እና ሲምፖዚየሞች በኮሮስፖንዳንስ ኮርሶች ማስተማር፤ የኦላይን ሴሚናሮች ማዘጋጀት፣ የማስተማር አገልግሎቶች፤ የቋንቋ ትምህርት አገልግሎቶች፤ ለባህላዊ _ እና _ ትምህርታዊ ዓላማዎች የሚሆኑ የኤግዚቢሽኖች ማዘጋጀት፣ ጽሑፎችን ማተም (ከማስታወቂያ በስተቀር)፤ የመጻሕፍት ህትመት፣ የኤሌክትሮኒክ _ ህትመቶችን በኦንላይን ማቅረብ (በቴሌማቲክ መንገድ ሊወርድ የማይችል) በኦንላይን መጽሄፎችን እና ወቅታዊ ጽሑፎችን በኤሌክትሮኒክ ማተም (ሊወርድ የማይችል)፤ በኦላይን የሕትመት አቅርቦት፣ የኤሌክትሮኒክ ጽሑፎችን ማተም፤ ከማስታወቂያ ጽሑፎች ውጪ ጽሑፎችን ማተም፤ የመጽሐፍ ብድር አገልግሎቶች ፤ የብሎግ አገልግሎቶች ናቸው።

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ  በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰውን የንግድ ምልክት በምዝገባ እንዲገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን  ካልቀረበ በስተቀር ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN Vol LXXXIV No 136-16/5/2017 (24 /1/2025 )